ስድስት ጉልቻ

ተፃፈ

በአስመላሽ ተፈራ

የመጨረሻ ረቂቅ

©ፋኖ ፊልም ፕሮዳክሽን

asmemika@gmail.com

2014 ዓ.ም

ሲን ፣

(የአዲስ አበባ ከተማ ገፅታ በከፍታ ምስል ይታያል)

ውጪ አቶ ለማ ግቢ በር አካባቢ-ጠዋት

ዴቭ

(የሚከራይ ቤት ፍለጋ ተደጋግፋ የቆመች የቆርቆሮ አጥር ያላት ግቢ በር ላይ ቆሞ ይጣራል)

እዚ ግቢ... (በቅርብ ሰው ያለ ስላልመሰለው ጮክ ብሎ ይጣራል) እዚ ግቢ...!

ለማ

ዘራፍ ወንዱ!

(ሸምገል ያለው የግቢው ባለቤት አቶ ለማ በአጥሩ አናት አጠናውን አስቀድሞ ብቅ ይላል)

ዴቭ

(ይደነግጣል)

ለማ

አይዞህ ይቺ የብር ሽለቆ ቀልድ እኮ አልለቅ አለችኝ (ዱላውን ይጥልና) እሺ ምን ፈለግክ

ዴቭ

የሚከራይ ቤት አለ

ለማ

ሞልቶ! . . . ግን ሴት ታበዛለህ እንዴ

ዴቭ

ኧረ በፍፁም እኔ መንፈሳዊ ህይወት ላይ ያለው ሰው ነኝ

ለማ

እና ቤቱን ባከራይህ እዚ ግቢ ምንም ሴት ይዘህ አትመጣም ማለት ነው

ዴቭ

ይኸው ይሄን ብርሀን አያሳየኝ ስሎት፤ ሴት የምትባል ፍጥረት ይገፎ አልመጣም ዶሮ እንኳን ብትሆን

ለማ

(ዝቅ ብለው ትልቅ ገጀራ ያነሱና)

ጥፋልኝ ከፊቴ!

ዴቭ

(በድንጋጤ ይጮሀል)

ለማ

ሴት ካላመጣህ ምን ትሰራልኛለህ ሂድና እዛ ሽንቱ የቀዘቀዘ አከራይ ፈልግ . . . . (በዴቭ ድንጋጤ ትንሽ ፈገግ ይሉና) አስደነገጥኩህ አይደል አይዞህ (የገጀራውን ስለት እያዩ) ይቺ የብር ሸለቆ ቀልድ እኮ አልለቅ አለችኝ

ዴቭ

(ድንጋጤው አለልለቅ ብሎት እያለከለከ) ስማ ይሄ በየቀኑ በሬ እየታረደልህ የለመድከውን የዱላና የገጀራ ቀልድህን እዛው ወታደር ቤት እሺ፤ ገና የምግብ ዋስትናውን ያላረጋገጠ ምስኪን ድሀ ህዝብ ላይ እንዲህ አይነት ቀልድ አይሰራም!

ለማ

(ዓይኑን አጠናግሮ ገጀራውን ዞር እያደረገ)

ዝም ላሰኝህ ወይስ ቀድመህ ዝም ትላለህ

ዴቭ

አልልም! አሁንስ በዛ!

(ኮብል ስቶን እያነሳ ወደ ወዳደቀው አጥር ይወረውራል)

ለማ

(ባስፈራራበት ገጀራ ፊቱን ከልሎ)

ልብ አርጉልኝ! . . በህግ አምላክ አጥሬን!

ዴቭ

የት የምታውቀውን ህግ ነው ደሞ አጥሬን ይላል እንዴ አጥር አልፎ ነገር እየፈለገ፤ ስማ! ፈሪ ከያዘው ሚሳዔል ደፋር የያዘው ድንጋይ ይሻላል እሺ፡፡ እንከባበር !

(ድንጋዩን ይጥልና ‹ና ደሞ ገለል› በሚለው ሀገርኛ የጀግና ሙዚቃ እየታጀበ በስሎው ሞሽን ሲራመድ ይታያል)

ሲን 2

ውጪ እነ ያሚግቢ-ረፋድ

(የግቢው በር ላይ የሚከራይ ቤት አለ የሚል ፅሁፍ ተለጥፎ ይታያል፡፡ ቁመናዋ አማላይ የሆነችው ሊንዳ የተጋለጠ ልብስ ለብሳ በበይበልጥ ሰውነቷ እንዲታይ ልብሷን ከደረቷ ወደ ታች እየሰባበችው ፣መልከ መልካሟ ያሚ በበስልኳ ስክሪን ፊቷን እየተመለከተች፣ አንባቢዋ መሲ መፅሀፍ እያነበበች ከግቢው ለመውጣት ወደ በሩ እየሄዱ ይታያል፡፡)

ዴቭ

(በር ያንኳኳል)

ሊንዳ

(በር ትከፍታለች)

ዴቭ

(ሲያንኳኳበት የነበረው እጁ የተገለጠው ደረቷ ላይ ያርፋል ሰውነቷ ቀልቡን ይነሳዋል ዓይኑ ሽውርር ይላል)

ሊንዳ

ሀቢብቲ የማነው ሸበላ በናታቹ (ደረቷ ላይ ያረፈውን እጁን እየተመለከተች) ትወርዳለህ ወይስ . . ታወርደዋለህ

ዴቭ

አይ ባወርደው ይሻላል

(እጁን ሲያወርደው የተሸዋረረው ዓይኑም ይመለሳል)

የሚከራይ ቤት አለ

ያሚ

ላንተ ነው

ዴቭ

አዎ ለኔ ነው

ያሚ

ላጤ ነህ

ዴቭ

አዎ

መሲ

ፍቅረኛ አለህ

ዴቭ

ኧረ የለኝም !

ያሚ

በቃ እኔ አሳየዋለው ሂዱ እናንተ

ሊንዳ

ኧረ ባክሽ! አከራይ ስለሆንኩኝ ልዩ ጥቅም ይገባኛል ያልሽ አልመሰለሽም ያውም ትላንት መጥተሽ ባልገዛሽው መሬት. ባልሰራሽው ቤት.

ያሚ

ወሬ አለብሽ ባክሽ

መሲ

ተዉ እንጂ ቆይ እኔ የምለው ሳምንቱን ሙሉ ተከራይ ሲመላለስ ንባቤን እያቋረጥኩ ሳሳያቸው ያልተጣላቹ አሁን ምን ተገኘ ብላቹ ነው እንዲ ጉዳቹን ላገር የምትዘረግፉት

ሊንዳ

ይሄኛው ሸበላ ነዋ በዛ ላይ ጥሩ የበር መቀርቀሪያ ይወጣዋል ና ግባ ሀቢቢ ቤትህን እናሳይህ

ዴቭ

እሺ

(ሙሉ ሰውነቱ ወደ ግቢ ገብቶ እጁን ብቻ ያወጣና ግቢው በር ላይ የተለጠፈውን የሚከራይ ቤት አለ የሚለውን ወረቀት ያነሳዋል)

በዛው ቦታ ላይ **የፊልሙ ርዕስ ይገባል**

ስድስት ጉልቻ

ሲን 3

ውጪ ደጅ ጠዋት

ተካበ

(መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ ውጪ የቆሙት ያሚና ዴቭን እያየ)

እሺ እሱ ነው አዲሱ ተከራይ የውል ወረቀት ይዜ መጥቻለው

ያሚ

አሪፍ ተከራይ ነው ያገኘነው እንትና ይባላል ማን ነበር ስምህ

ዴቭ

ዳዊት እባላለው የኔ እመቤት

ተካበ

እሺ ዳዊት እንዴት ነው ቤቱን ወደድከው

ዴቭ

አው በጣም ወድጀዋለው

ተካበ

ያዝ በል ይቺን አንብብና ስምህን ፅፈህ ፈርም . . . እንግዲህ ግቢውን አደራ! አንተ ብቻ ነህ ወንድ ያለኸው

ሲን 4

ውጪ እናኑ ግቢ የዴቭ የቀድሞ ግቢ በር ላይ

እናኑ

(በር ስትከፍት ሜላትን ታያታለች) ሜላትዬ የኔ ቆንጆ ልጅ .

. . (እንደልጅ ትስማታለች)

ሜላት

እናንዬ ዴቭ አለ

እናኑ

(አንገቷን እየደፋች) አይ የለም

ሜላት

የት ሄዶ ነው ስልክም አያነሳልኝም እኮ

እናኑ

ቤት ለቂል

ሜላት

ምን! ማለቴ እንዴት

እናኑ

እኔም ትላንት ነው ያወቅኩት ቁርስ ሰርቼለት በሩን ስከፍት ዕቃውም እሱም የሉም

ሜላት

እሺ የት እንደሄደ አታውቂም

እናኑ

እየነገርኩሽ ሜላትዬ

ሜላት

እናንዬ አትንገሪያት ብሎሽ ነው አይደል እኔስ ልጅሽ አይደለው አላሳዝንሽም

እናኑ

እንዴት አታሳዝኚኝ ልጄ እኔ የሄደበትን ባውቅ ሺ ጊዜ ተቀይሞኝ ይቅር እንጂ ካንቺ እንዴት አድርጌ እደብቅሻለው ባያድለው ነው እንጂ አንቺን የመሰለች ልጅ .... በይ ግቢ አሁን ቆንጆ ቡና አፈላልሻላው

ሜላት

አይ ልሂድ (ጉንጯን ስማት እያለቀሰች ትሄዳለች)

እናኑ

አይ ዳዊት ! ያላደለህ!

ሲን 5

ውስጥ ዴቭ ቤት ከሰዓት

(ቤት ውስጥ ዕቃዎቹ ከቀዳሚው ትዕይንት በተሻለ በወግ በወግ ተቀምጠው ይታያሉ)

መሲ

ቤትህ በጣም ነው ያማረበት ከእንግዲህ በኋላ የወዳደቀ ካልሲ በፌስታል ተገዝቶ የተራረፈ ምግብ

ያልተነጠፈ አልጋ

ሊንዳ

አልጋውን እንኳን እኔ በየቀኑ እየመጣው ስለማነጥፍለት አታስቢ ምንም አይበላሽም

መሲ

አዪ... አንቺ በየቀኑ ከመጣሽማ እንኳን አልጋው ልጁም ተበላሽቶ መቅረቱ ነው

ሊንዳ

ወሬ አለብሽ ይሄን የመሰለ ሽበላ ቤቴ አስገብቼ ሀቢቢዬ

(ታፋውን በእጇ ቸብ ታደርገዋለች . . እነያሚ ይስቃሉ)

ዴቭ

እንዴ ... ምንድንነው መሲ ያታዊ ጥቃት እየደረሰብኝ እኮ ነው ዝም ትያለሽ እንዴ

ያሚ

(ከውጪ እየገባች) እ ሰዎች ሰውየው ሄዷል

ዴቭ

እሺ የአረጋውያን መርጃ ጭራሽ ስሜም ጠፋሽ አይደል

ያሚ

የስራው ባህሪ ነው ምን ታደርገዋለህ ይልቅ አዲሱን ቤት ቡና አፍልተን ብንመርቀው ምን ይመስላቿል

መሲ

በጣም ጥሩ ሀሳብ ብዙነሽ በቀለ ለበዓሉ የምታፈላለትን አይነት ኪናዊ ለዛ የተላበሰ ቡና ብናፈላ

ሊንዳ

ዝም በይ ባክሽ አዛ ዑመክ ነዐል ጡዝ ጡዝ ኪናዊ ምናምን እያልሽ ዕድር ትጠሪያለሽ እንዴ የምሬን ነው መቼም እንደ ለቅሶ ቤት ቡና በጋራ እንጠጣ እንደማትሉ ነው

መሲ

እንደውም እኔና እሱ ብቻ ቁጭ ብለን መፅሀፍ እያነበብን ብናፈላ ጥሩ ይመስለኛል

ሊንዳ

ቢሆን እኮ ደስ ይለኝ ነበር ግን መፅሀፍ ካነበባቹ አታፈሉም ካፈላቹ ደግሞ መፅሀፍ አታነቡም ስለዚህ እኔ እና እሱ ነን ማፍላት ያለብን ባይሆን ሁለተኛ ሶስተኛ ሲፈላ እጠራቿለው አይደል ሀቢቢዬ

መሲ

እንደውም ዕጣ እናውጣ (ወረቀት ላይ ስማቸውን ትፅፋለች)

ያሚ

በሉ በሉ እኔ እንደዚህ አይነት ሽሚያ ቅሚያ ግፊያ አይመቸኝም የኔን ስም እንዳትፅፊ

ዴቭ

አንቺ ብታፈይልኝ ግን ደስ ይለኝ ነበር

ያሚ

ሲጀመር አልችልም ብችል እንኳን በዚህ አይነት ሁኔታ በፍፁም

መሲ

እሺ ዕጣውን አውጪልኝ

ያሚ

(ከጥቅሉ ወረቀት አንስታ ትፈታዋለች)

መሲ ያንቺ ስም ነው የወጣልሽ . . ሊንዳ ነይ ቀጥይ ወደ ውጪ

ሊንዳ

እስኪ ሁለቱም ላይ ስሟን ፅፋ ሊሆን ይችላል ቼክ ይደረግልኝ

ያሚ

ኧረ ዝም በይ ባክሽ መሲ ደግሞ ከመች ጀምሮ ነው እንዲ የምታደርገው ይኸው ቀሪው ላይ ያንቺ ስም ነይ ውጪ አሁን

(ያሚና ሊንዳ ይወጣሉ)

ሲን 6

ውስጥ ተካበ ቤት ምሳ ሰዓት

ተካበ

ያዥ ይሄን ውል ጥሩ ቦታ አስቀምጪው! ብታይ አንቺ ጋር ለመምጣት ቸኩዬ ተከራይ ላይ ልፈርም ወይም አከራይ ላይ ምንም የማውቀው ነገር የለም

ሀና

ተኬ እንዲህ አይነት ነገርማ ጠንቀቅ ነው ማለት ያለብህ ውል እኮ ነው

ተካበ

ምን አባቴ ላድርግ ጥንቅሼ ምሳዬን ሳልበላ ሄጄ ራበኝ ለዛ እኮ ነው ስከለፈለፍ የመጣሁት

ሀና

ቀንጆ ምሳ ሰርቻለው (ልታመጣ ትነሳለች)

ተካበ

(በቀኝ እጁ እጇን ይይዛትና) ምግብማ ሞልቷል አምላክ መች ነሳን (በግራ እጁ ይኮረኩራታል)

ሲን 7

ውስጥ ዴቭ ቤት ከሰዓት

መሲ

(*መፅሀፍ እያነበበች ቡና ስታፈላ ይታያል*)

ዴቭ

በነገርሽ ላይ አንባቢ ሴት በጣም ነው የምወደው

መሲ

(*መፅሀፉ ላይ ተመስጣ*)

አይደል እ..

ዴቭ

እቺ ደሞ ዘነበ ወላን ልሁን አለች

መሲ

ዘነበ ወላ ስትል ሰማው

ዴቭ

አው በጣም የምወደው ደራሲ ነው በተለይ ስለ ባህር ውስጥ እንስሳት ሲተነትን እዛው አብሯቸው የሚኖር እንጂ መሬት ላይ ቤት ያለው አይመስልም

መሲ

አው በጣም ደስ ይላል ታዲያ አንድ ሶስት *መፅሀፎቹን* እኮ አምጥቼልሀለው ለምን እያነበብክ ምርጥ ጊዜ አናሳልፍም

ዴቭ

ማለት ምን አይነት ምርጥ ጊዜ

መሲ

ሁለታችንም አንድ አንድ *መፅሀፍ* ይዘን ፀጥ ብለን እያነበብን የምናሳለልፈው ምርጥ ጊዜ

ዴቭ

በለው የሰው *መመሳሰል* አይገርምሽም እኔም እንዲህ አይነት ባህሪ አለኝ (ድምፁን ዝግ አድርጎ)

ቀልደኛ!

መሲ

እኔ ይቅርታ አድርግልኝና አጠገቤ *መፅሀፍ* ሳይዝ እደሚቀመጥ ሰው የሚጨንቀኝ ነገር የለም

ዴቭ

ይቅርታ አታርጊልኝና እኔ ደግሞ አጠገቤ *መፅሀፍ* ይዞ እንደሚቀመጥ ዝጋታም ሰው የሚጨንቀኝ ምንም ነገር የለም

መሲ

እንዴት እንዲህ ትላለህ

ዴቭ

እስከሚገባኝ ድረስ ከሰው ልጅ በላይ ምንም ክቡር ነገር የለም አንዳንድ አንባቢ ነን የሚሉ ሰዎች ግን ወረቀትን ከሰው ልጅ አብልጠው ጊዜያቸውን ከመፅሀፍ ጋር ብቻ ሲያጠፉ ያናዱኛል የምናነበው እኮ ከሰው ጋር ለመኖር ነው መሆን ያለበት

መሲ

በርግጥ ንግግርህ እውነትነት አለው ይህን የምልህ በራሴም ህይወት የማስተውለው ስለሆነ ነው አንዳንዴ የሰው ድምፅ እስከመጥላት እደርሳለው ይሄ ደግሞ ጤናማ ስሜት አይመስለኝም

ዴቭ

ታዲያስ! አንቺም እስካሁን ድረስ ያካበትሽው ዕውቀት በቂ ስለሆነ ካሁን ወዲህ ከሰው ጋር መኖር ብትጀምሪ ጥሩ ይመስለኛል

መሲ

እስኪ እሞክራለው

ዴቭ

አሁን ብትጀምሪ ምን ይመስልሻል መፅሀፉን ታስቀምጪና እዚችጋ ከሰው ጋር ትቀመጫለሽ ማለት ነው

መሲ

(አጠገቡ ትቀመጣለች)

ዴቭ

መሲዬ

መሲ

አቤት

ዴቭ

ፊትሽ ላይ የሚነበበው ትህትና ከዕድሜሽ በላይ የተሸለምሽው እርጋታ ብቻ ምን አለፋሽ በሰዓታት ጊዜ ውስጥ የሳቡኝ በርካታ መልካም ባህሪያትን አንቺ ላይ አስተውያለው

ዴቭ

ፈጥኖለው ግን የተሳሳትኩ አይመስለኝም የሰው ልጅ ገላና መልኩ አላፊና ጠፊ መሆናቸውን ተገንዝቦ መመኪያው ማድረግ ያለበት ፈጣሪና አዕምሮው ውስጥ ያለውን ዕውቀት ነው ብዬ አስባለው አይመስልሽም

መሲ

አብዛኛውን ሀሳብህን እጋራህና በዕውቀት መመካትና የዕውቀት ዘላለማዊነት አስመልክቶ ያነሳኸው ሀሳብ ላይ

ዴቭ

(እጇ ላይ ያለውን መፅሀፍ ተቀብሎ ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጠውና መዳፏን በጣቶቹ መደባበስ ይጀምራል)

መሲ

(እጇን የምታደርገው ነገር ግራ ገብቷት ድጋሚ መፅሀፉን አንስታ ትይዘዋለች)

ዴቭ

(በድርጊቷ ፈገግ ብሎ መፅሀፉን ተቀብሏት ያስቀምጠውና እጇን ይይዛታል)

(እየተያዩ ጥቂት ዝምታ ይሰፍናል)

መሲ

(ትንፋሷ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ይጀምራል)

አይ እንደዚ መሆን የለበትም (ተነስታ ትወጣና ተመልሳ ትመጣለች)

ይቅርታ ትንሽ ስሜታዊ ሆኜ ነው አሁን ስለተረጋጋው ካቆምንበት መቀጠል እንችለላለን

ዴቭ

(ድጋሚ እጇን መደባበስ ይጀምራል)

መሲ

አይ አይሆንም እንደዚ መሆን የለበትም(ድጋሚ ተነስታ ትወጣና ተመልሳ ትመጣለች)

አሁን እንኳን አልተረጋጋሁም ከአባቴ እጅ ውጪ በዚ መልኩ እጆቼን የደባበሳቸው ወንድ እንደሌለ ለመንገርና መፅሀፌን ለመውሰድ ነው የመጣሁት

ዴቭ

አቤት ምላስ! አቤት ምላስ! ከአስር አቋርጠህ ግን እንዲህ መራቀቅ አይከብድም ኧረ አንተ ሰውዬ እረፍ! . . ዓይንህ ይቅበዘበዛል! ምላስህ ይንበለበላል! እንደው ምን ይሻልሀል፤ እስኪ እዚ ቤት እንኳን ሴት ሳትጎትት ኑር

ሲን 8

ውሰጥ ተካበ መኝታ ቤት ምሽት

(ሀና እና ተካበ ፍቅር ሰርተው አንደጨረሱ በሚገልፅ ፊት አልጋ ላይ ተኝተው ከደረት በላይ ገላቸው ይታያል)

ሀና

ተኪዬ እስኪ ስለቤተሰቦችህ ንገረኝ

ተካበ

ምን ቤተሰብ አለኝ ብለሽ ነው ምድረ ጭቅቅታም የገጠር ልጅ ብቻ ናቸው አንድ እንኳን ቤተሰብ ብዬ ሰው ፊት የማቆመው ዘመድ የለኝም የኔ ቤተሰቦች አንቺ ያሚዬ....

ሀና

(በንዴት ጀርባ ሰጥታው ትተኛለች)

ተካበ

ምነው ጥንቅሼ

ሀና

ከኔ ጋር ሆነ ስለ ሌላ ሴት ባታወራልኝ ደስ ይለኛል

ተካበ

ምክንያቱስ

ሀና

የኔ ብቻ እንደሆንክ ነው ማሰብ የምፈልገው

ተካበ

(እንደ ህፃን ያጫውታታል) ኧረ ምንድን ነው እሹ

ሀና

ተኬ ሙት የምሬን ነው

ተካበ

ሂጅ ወደዛ! አጉል ፍቅር ፍቅር አትጫወቺ

ሀና

አልተጫወትኩም! የቤቴ አባወራ እንዳንተ ሞገስ ያለው ቢሆን ደስ ይለኛል፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው አካልህም መንፈስህም ካንድ አይረጉም

ሲን 9

ውስጥ መሲ መኝታ ክፍል ምሽት

መሲ

(መኝታ ክፍል ውስጥ ጋደም ብላ ዕንቅልፍ ቸግሯት ስትቁነጠነጥ . . . ትራሷን አቅፋ በሀሳብ ጭልጥ ስትል . . . ከዛም መፅሀፍ አንስታ ልታነብ ስትል ከዚ ቀደም ባለው ትዕይንት ላይ የነበረው የዴቭ ምስል ከተመስጧዊ ዕይታው ጋር የመፅሀፉ ገፅ ላይ ሲመጣባት ይታያል)

ወይኔ መሰረት ምን እየሆንኩኝ ነው አሁን መፅሀፍ ስገልጥ መጣብኝ ብል ማን ያምነኛል ድሮ የቀረ ፍቅር

(የግቢ በር መከፈት ድምፅ ይሰማል)

ሲን 10

ውጪ ግቢ ውስጥ እኩለ ለሊት

ሊንዳ

(ሁሌም የግሮሰሪ ደምበኞቿን ሸኝታ በምትመጣበት ሰዓት ከስራ መልስ የግቢውን በር ከፍታ ስትገባ ይታያል)

(ወደ ቤቷ ልትገባ ትልና ሀሳቧን ቀይራ ወደ ዴቭ ቤት ትሄዳለች)

መሲ

(የመጋጃውን ጨርቅ ገለጥ አድርጋ በመስኮቱ በኩል ትመለከታታለች)

(ድምጿን ዝግ አድርጋ ለራሷ ታወራለች) እንዴ በዚ ሰዓት ወዴት እየሄደች ነው ተመለሽ አንቺ ባለጌ! (ሳታስበው ድምጿ ይጮሀል) አትመለሽም!

ሊንዳ

(የዴቭን በር ልታንኳኳ ስትል በሰማችው ድምፅ ከእንቅስቃሴዋ ይገታትና አንገቷን ብታዟዙርም ድምፁ ወደ መጣበት አካባቢ ዘወር ብላ ሰው ፈልጋ ታጣለች)

አሁዝቢላሂ መነ ሸይጣን

መሲ

(ከመስኮቱ ስር በመሳቀቅ አፏን አፍና ተቀምጣ ይታያል)

ሲን ፲፩

ውስጥ ዴቭ ቤት እኩለ ሌት

(ብቻውን ማደር ያልለመደው ዴቭ አገጩን እጁ ላይ አስደግፎ በድብርት ስሜት ይዘፍናል)

ባዶ ቤት ለብቻ /2*/

(በር ይንኳኳል)

ሊንዳ እንዳትሆን ብቻ/2*/

(የመዝጊያ በር ላይ ያለውን ቀዳዳ ለመድፈን የተወተፈውን ወረቀት ያነሳና አጮልቆ ወደ ውጭ ሲመለከት ካሜራው በአይኑ ያየውን ምስል ያስመለክተናል)

ዴቭ

(ሰውነቱን ከላይ እስከታች ነዝሮት ርግፍግፍ ካለ በኋላ ወረቀቱን ደፍኖ ራሱን ያረጋጋና በሩን ይከፍታል)

እንዴ ሊንዳ

ሊንዳ

እንዴት ነው ሀቢቢ ለመድከ

ዴቭ

አው ለምጃለው ቤታቹ ግን ትንሽ ብርድ ብርድ የሚለው ነገር አለ

ሊንዳ

የሀገሩን ብርድ በሀገሩ ሴት ይልሀል አሁን ነዋ

ዴቭ

ታዲያ ግቢ እንጂ ምነው በሩ ላይ ቆምሽ

ሊንዳ

የንዋይዬን ዘፈን ታውቀዋለህ

ዴቭ

ምን የሚለውን

ሊንዳ

ምነው በደጅ አሆይ ጎራ በይ እንጂ

ዴቭ

(በፈገግታ ይቀበላታል) አሆይ

ሊንዳ

ምነው በበሩቁ

ዴቭ

አሆይ

ሊንዳ

እየናፈቁ.... (የገጠር ወንዶች እንደሚያደርጉት በእጇ ታፋውን በሀይል ቸብ አድርጋ ትመታዋለች)

ዴቭ

ሂጅ አንቺ እንዴ... እቺ ምን አይነት ዕብድ ነች ሆ!

ሊንዳ

(የቤቷን በር እየከፈተች) በል ደህና እደርልኝ ሀቢቢ እምጽፅ

ዴቭ

እሺ (እየነደደው ፈገግ ይላል)

ሊንዳ

ነገ እንፈላለግ እሺ ሀቢቢዬ (በሩን ትዘጋዋለች)

ዴቭ

ሀቢቢ ሀቢቢ ትላለች ዝምብላ የሆነማ ንፋስ ስባለች ዳዶዋን አላልተው ነው የላኳት. . . . አሁን ይሄ የተረገመ ዘልዛላ ምሽት እንዴት እንዴት ይነጋል ነው ትልቁ ጥያቄ አይ ሊንዳ! እንደው አንቺስ አይንጋልሽ! አሳይተሽ ትነሽኝ (በሩን ይዘጋዋል)

ሲን 12

ውስጥ ያሚ ኮስሞቲክስ ሱቅ ጠዋት

ያሚ

(ከተለያዩ የጥፍር ቀለሞች አንድ አንድ ጥፍሯን እየተቀባች መልሳ ዲስፕሌይ ላይ ታስቀምጠዋለች)

ዴቭ

(ድንገት ሱቅ ውስጥ ይከሰታል)

ሄለው

ያሚ

(ደንግጣ ጥፍር ቀለሙን ትጥለዋለች)

ዴቭ

አይዞን የምን መደንገጥ ነው

(ጥፍር ቀለሙን አንስቶ ጥፍሯን ሊቀባት እጇን ይይዛታል)

ያሚ

ምን አይነቱ ሰላቢ ነው በፈጣሪ . . አንተ! ኮቴ የለህም እንዴ

ዴቭ

ድሮ ድሮ ነበረኝ አሁን ግን በጣም በእግሬ ከመሄዴ የተነሳ አልቋል

ያሚ

(ከድንጋጤዋ ወጥታ ትስቃለች)

ዴቭ

(ቅሽባ ላይ ስለደረስኩብሽ ደንግጠሻል አይደል)

ያሚ

ስነ ስርዓት ሰውዬ ድምፅህን ቀንስ

ዴቭ

ሲመስለኝ ይሄን አይነት አቀባብ ፋሽን ያደረጋቹት እናንተ ሳትሆኑ አትቀሩም የቀረውን እኔ ልቀባልሽ እችላለው

ያሚ

ደስ ይለኛል

(ጣቶቿን እጁ ላይ ታስቀምጥለታለች)

ዴቭ

(ቀና ብሎ እየተመለከታት) ጥሎብኝ እጅግ በጣም የውበት አድናቂ ነኝ በተለይ እንዳንቺ አይነት በፈገግታ የታጀበ ውበት ደግሞ ምንም እንዳላስብ ነው የሚያደርገኝ

ያሚ

ሰውዬ እያሰመጥከኝ ነው ታውቆሀል

ዴቭ

የምሬን እኮ ነው የምልሽ ሴት ልጅ ሺ ጊዜ አስተሳሰቧ ሊመጥቅ ይችላል ደግሞም ለዕቅፍ ሞላ ብላ አልጋ ልታሞቅ ትችላለች ግን መልኳ ካላማረ ምን ዋጋ አለው ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል አይደል የሚባለው

ያሚ

(ራሷን በአዎንታ እየነቀነቀች ደስ ደስ ይላታል)

ተካበ

(ወደ ሱቁ ይገባል)

ዴቭ

(መቀባቱን ጨርሶ እጁን ስሞ ጭኗ ላይ ያስቀምጠዋል)

ያሚ

(የዴቭ ጨዋታ መስጧት ፊት ለፊት እያያት ያለውን ተካበን ሳታይ ንግግሯን ትቀጥላለች) ደሞ አቀባብህ ያምራል የት እንደለመድከው ትናገራታለህ አዎ ፖሊስ ጣቢያ ሲገርፉህ ትናገራታለህ! አንተ ልክስክስ! ተኬ አስወጣልኝ ከዚ!

ተካበ

(አንገቱን ደፍቶ በንዴት ይተነፍሳል)

ዴቭ

(ሹልክ ብሎ ይወጣል)

ሲን 13

ውጪ መፅሀፍ ተራ ቀን

መሲ

(ጭራ እያነፈሰች መፅሀፍቶቹ አቧራ እንዳይነፍስባቸው ስታደርግ ይታያል ሱቁ ውስጥ የጥላሁን ገሰሰ አይ ዘመን አይ ጊዜ የሚለው ዘፈን ተከፍቶ ይሰማል)

ሳሚ

መሲያችን የዕውቀት እናታችን

መሲ

አንተ አፈ ቂቤ አለህ ለመሆኑ

ሳሚ

ታዲያስ ! ለድንቁርና እጅ አልሰጥም እንዳልኩ አለሁልሽ

መሲ

እስኪ አንድ ቀን እንኳን ግዛኝ ሁሌ ልቤን እንዳደረቅከኝ ስትሄድ ቅር አይልህም

ሳሚ

መሲዬ እኔ እኮ የቅርብ ጊዜ መፅሀፍ ብዙም ስለማላነብ ነው እኔ የምፈልጋቸው የድሮ መፅሀፍቶች ደሞ አንቺ ጋር የሉም

መሲ

እስኪ አንተ ይሄን መፅሀፍ እገዛሻለው በለኝና እኔ ጋር ከታጣ ልቀጣ

ሳሚ

እሺ መንኳኳዕ ዘይፈለዮ አፀው የሚለው መፅሀፍ አለሽ

መሲ

የጠቅላይ ሚኒስትሩ

ሳሚ

አዎ የአቶ መለስ ዜናዊ . . . ካገኘሽልኝ ባልሸኝ ዋጋ እገዛሻለው

መሲ

እስኪ የአባቱ ጓደኛ ጋር ካለ ጠይቄልህ ልምጣ እያየህልኝ

(ትሄዳለች)

ሳሚ

(ራቅ ማለቷን ያይና የሚፈልገውን መፅሀፍ አንስቶ ጀርባው ውስጥ ይደብቅና በሸሚዙ ከልሎ ይቀመጣል)

በቀለ (መፅሀፍ ገዢ)

በቀቀን የሚለው መፅሀፍ አለህ

ሳሚ

ይቅርታ ምን አይነት መፅሀፍ ነው

በቀለ

ምን አውቃለው የደራሲው ስም ሲሳይ ነው እሱን እንኳን የአንቱ ስም ስለሆነ አልረሳውም

ሳሚ

የሲሳይ ንጉሡ ሰመመን የሚለውን መፅሀፍ ነው የፈለግከው መሰለኝ

በቀለ

እ... አመጣኸው

ሳሚ

ይኸው

በቀለ

(ዋጋውን አይቶ ይከፍላል)

አዬ ሳይቾግር ጤፍ ብድር አለ

ሳሚ

ምነው ችግር አለ

በቀለ

ምን እባክህ አንዲት አንባቢ ልጅ በፍቅር ቀርቢያት ተሰቃየሁ

ሳሚ

ምነው በደህና

በቀለ

መድኃኒት ተፅፎለት በየፋርማሲው እንደሚዞር በሽተኛ ለኔም የመፅሀፍ ርዕስ እየፃፈች ታንከራትተኛለች፤ ብላ ብላ ዛሬ ደግሞ ይሄን በቀቀን የሚለውን መፅሀፍ

ሳሚ

ሰመመን

በቀለ

አዎ ሰመመን . . እና አንብበህ ሙሉ ታሪኩን እንድትነግረኝ ስላለችኝ እባክህ የኔ ወንድም ካነበብከው ሙሉ ታሪኩን አጠር አድርገህ ብትነግረኝ

ሳሚ

አይ አላነበብኩትም

በቀለ

ታዲያ የማታነብ ከሆነ ለምን ትሸጣለህ ቲማቲም ምናምን ብትነግድ አይሻልህም አሁን ብትነግረኝ ምን ትሆናለህ ክፉ!

(ይሄዳል)

ሳሚ

(ሰውዬውን ከሸኘ በኋላ መፅሀፎቹን ሲያይ አሁንም ይጓጓና አንድ መፅሀፍ በሆዱ በኩል ቀበቶ ውስጥ እንደ ሽንጠ መሲ ትመጣለች)

እ መሲዬ ተገኘ

መሲ

ካገኘኸው ለኛም ግዛልን ብለውህል

ሳሚ

(ይስቃል) ግድ የለሽም ወደ መርካቶ ልፈልገው አላጣም ደሞ ሰመመን ተሸጧል ይኸው ብሩ የማላስቸግርሽ ከሆነ ትምህርት ሲዘጋ አብሬሽ መዋል እችላለው

መሲ

የምታስከፍለኝ ከሆነ ግን ይቅርብኝ

ሳሚ

እሺታሽ ከክፍያም በላይ ነው እ

መሲ

እሺ

ሳሚ

በጣም አመሰግናለው ቻው መሲዬ

ሲን 14

ውስጥ ያሚ ሱቅ ቀን

ተካበ

በገዛ አልጋዬ ላይ ከሌላ ወንድ ጋር እንደማገጥሽብኝ ነው የምቆጥረው ደሞ አሪፍ ተከራይ አገኘው ስትይኝ አለመጠርጠሬ ጭራሽ ጎረምሳ ቤቴ ድረስ አንቺ ማጋጣ

ያሚ

ስማ ! ወር ሙሉ ቅምጦችህ ጋር ስትሽከረከር ማገጥከብኝ ብዬህ አውቃለው ንገረኝ

ተካበ

ኧረ ቀስ የቃቄ ውርድወት ጭራሽ እንደኔም መሆን አማረሽ አሁን ሱቄን ለቀሽ ውልቅ

ያሚ

(ትደነግጣለች) እንዴ ተኬ ደሞ ከመሬት ተነስተህ ስሜታዊ የምትሆነው ነገር አለ (የኮስሞቲክስ ቤቱን በር ዘግታ ወደ ተካበ ትሄዳለች)

ተካበ

ሴትዮ አማርኛ ትሰሚ እንደው ተናግሬያለው ውልቅ በይ አልኩሽ ውልቅ በይ

ያሚ

(አይኗን እያስለመለመች ትነካካዋለች)

ተካበ

(ቁጣው ወደ ፈገግታ እየተቀየረ) በቃ ውልቅ በይ ስትባይ አትሰሚም አይደል

ሲን 15

ውስጥ እናኑ ግቢ ቀን

ማርታ

(በሩን ትቆረቁራለች)

እናኑ

(በር ትከፍታለች)

ማርታ

(አልፋ ልትገባ ስትል እናኑ በሩን በእጇ ይዛ መንገድ ትዘጋባታለች)

እናኑ

ዳዊት ቤት ለቋል

ማርታ

ምን! ለኔ ሳይነግረኝ አይደረግም

እናኑ

እንግዲህ ተደረገ

ማርታ

በፍፁም አይሆንም !እንደማንኛዋም ሴትማ እሱ በፈለገ ሰዓት ዞር በይ ሊለለኝ አይችልም ማርታ እኮ ነኝ ማርቲ

እናኑ

አሀ ነሽ እንዴ

ማርታ

አዋ ! ስንት ወንድ እንዳስለቀስኩ አያውቅም

እናኑ

አይ እንደሱስ ከሆነ የእጅሽን ነው ያገኘሽው

ማርታ

ትርፍ ወሬ አልፈልግም የት እንደሄደ ነግሮሻል አልነገረሽም

እናኑ

ለጭን ገረዱ ያልተናገረ ለኔ ይነግረኛል ብለሽ ነው

ማርታ

የገባበት ገብቼ ማን እንደሆንኩ አሳየዋለው እኔ ማርታን ማንም ጥሎኝ ሄዶ አያውቅም

እናኑ

ምን ትመስላለች የሆነች ሙዝ አቋም ! አይ ልጄ . . ለመኖሪያ ብለህ ተከራይተህ .ግቢውን ፔንሲዮን ማድረግህ ሳያንስ ከወጣህም በኋላ ቅሬታ ሰሚ አድርገኸኝ ትቀር አሂሂሂ....

ሲን 16

ውጪ ግቢ ውስጥ ቀን

ሊንዳ

(ገንፎ በጎድጓዳ ሰሀን ይዛ ወደ ዴቭ ቤት ትሄድና እያንኳኳች) የሀቢቢ ቁርስ ደርሷል ሀቢቢ.... ሀቢቢ.... አንተ ሀቢብ

(በሩን ቼክ ስታደርገው ተዘግቷል)

ወይኔ ድካሜ ከንቱ ሆነ ማለት ነው

ዴቭ

(ከየት መጣ ሳይባል ከጀርባዋ ከተፍ ይላል)

አይሆንም በፍፁም ከንቱ አይሆንም የሀቢብቲ

ሊንዳ

በጠዋቱ ተነስቼ ቁርስ ሰርቼልህ የሌለህ መስሎኝ በጣም ደብሮኝ ነበር

ዴቭ

ሰባት ሰዓትን ጠዋት አልሽው

ሊንዳ

ታዲያስ ለሊት ሰባት ሰዓት ለሚገባ ሰው ጠዋት ነው . . እና ገንፎዬን ብላልኛ

ዴቭ

እበላልሻለው ሀቢብቲዬ ገንፎሽን እበላልሻለው እ.. ደሞ ደሞ ገንፎሽንም እበላልሻላው

ሊንዳ

(በፈገግታ)

ምላስሽ እኮ ረዥም ናት በል በዚች ወገብህን ጠግነህ ቆየኝ ሻወር ወስጄ መጣው . . . እስኪ ጉድህን አይልሀለው

(ዳሌዋን እያገለባበጠችው ወደ ከፍሏ ትገባለች)

ዴቭ

(ሊንዳ እስክትገባ አይኑ መቀመጫዋ ላይ ይንከራተትና ገብታ በሩን ስትዘጋው ዓይኑ ዕንባ ማቅረር ይጀምራል)

አዝናለው ያሚዬ! በጣም አዝናለው የኔ ውብ ፅጌዳ !ዛሬ ፍቅሬን ገልጬልሽ ዛሬውኑ ስወሰልትብሽ ከፍተኛ ሀዘን ይሰማኛል፤ ነገር ግን ሀዘንሽን በባዶ ሆዴ አልቋቋመውምና የእዝን የመጣልኝን ገንፎ ልንፋው

(በማንኪያው ተለቅ ተለቅ አድርጎ ይጎርስና ይጨርሳል . . (ከዛም ሰሀኑን ይዞ ሄዶ የሊንዳ በር ደጃፍ ላይ ያስቀምጥና) እንዲህ ትኩስ ገንፎ እንዳበላሽኝ ብድር መላሽ ያርገኝ ሊንዳ ሙች በጣም ከባድ ሰው ነሽ እሱ ይሁነኝ እንጂ ደሞ እንደዚ አይባልም ለካ (እየዘፈነ ወደ ቤቱ ይገባል)

እኔንጃ እኔንጃ እኔንጃልኝ

ተፈቅፍቄ የምነሳ መሰለኝ

ኧረ እኔስ እንጃ እንጃልኝ

ሲን 17

ውስጥ ዴቭ ቤት ቀን

(ሊንዳ ዴቭ ዕቅፍ ውስጥ ተሸጉጣ ይታያል)

ሊንዳ

ሀቢብቲ

ዴቭ

ወዬ

ሊንዳ

የማትፈልገውን ነገር እንድታደርግ አልገፋፋሁህም አይደል

ዴቭ

ኧረ በፍፁም እንደውም እስከዛሬ ያንቺ አይነት ስሜቷን በግልፅ የምትናገር ሴት ነበር የምፈልገው ነገር ግን እንዲህ አማላይ ከሆነ ሰውነት ጋር አገኘዋለው ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ሊንዳዬ ለሰው ልጅ በዚህ ነገር ከመታደል በላይ ምን አስደሳች ነገር አለ

ሊንዳ

አፌ ቁርጥ ይበልልህ ሀቢቢዬ! እቺን ቀን ለስንት ዘመናት እናፍቃት እንደነበር አታውቅም፡፡ ስፀዲ ሆኜ ፈጣሪዬ የሀገሬን ጎረምሳ ደረት ሳልንተራስ እዚ በረሀ ላይ እንዳታስቀረኝ እለው ነበር› ይኸው የለመኑትን የማይረሳ አምላክ ፀሎቴን ሰማኝ

ዴቭ

ለሱ ምን ይሳነዋል

(እንዳይከፋት ብሎ ስሜቷን ተጋብቶ ያስተዛዝናታል)

ሊንዳ

ብታይ ሀቢቢዬ ገና የአስራ ዘጠኝ አመት ልጅ እያለው ነው ወደ ስፀዲ የሄድኩት አስር አመት ሙሉ ከአንድ ቤት ሳልወጣ ለጨረጨሰች የአረብ አሮጊት ሽንት ጨርቅ ስቀይርና ሩዝ ስቀቅል ነው ወጣትነቴን የጨረስኩት ኢትዮጲያ ስመለስ ደሞ እናንተ ትናንሽ ሴቶች ላይ ነው አይናቹ

ዴቭ

ኧረ እኛ...

ሊንዳ

(በጣቷ ከንፈሩን ይዛ ንግግሩን ታስቆመዋለች)

ስስ....ሀቢቢዬ

ዴቭ

ወዬ

ሊንዳ

የባከነው የወጣትነት ጊዜዬ እንዳይቆጨኝ አድርገኝ!

ዴቭ

እንዴት አድርጌ

ሊንዳ

እሱን ለኔ ተወው

(በሩን ልትቆልፈው ትሄዳለች)

ዴቭ

አስር አመት ያልተነካ ዕቃ ተመንጭቆም የሚነሳ አይመስለኝም

ሊንዳ

(በሩን ቆልፋ መጥታ ፊት ለፊቱ ተጋርዳ ትቆምና ልብሷን ከላይ ጀምራ ታወልቃለች)

ዴቭ

(ሰውነቱ በፍርሀት ወባ እንደያዘው መንቀጥቀጥ ይጀምራል)

ሊንዳ

የሀቢቢ አለቀልህ እንግዲህ

ዴቭ

(ዘፍ ብላ ላዩ ላይ ልትከመር ስትል በነን ሾልኮ በሩን ከፍቶ ይሮጣል)

ሊንዳ

(በወደቀችበት እየተንከባለለች) አይሆንም ሀቢቢ እሳት ላይ ጥለኝኝማ አትሄድም

ሲን 18

ከውጪ ወደ ውስጥ መሲ ቤት ቀን

መሲ

(ከስራ መልስ በአንድ እጇ ለእራት የሚሰሩ ነገሮች በሌላኛው እጇ ደግሞ እንደተለመደው መፅሀፍ ይዛ የቤቷን በር ከፍታ ከመግባቷ ዴቭ ሲሮጥ ትሰማና ዘወር ትላለች)

ዴቭ

(እየተንደረደረ ይመጣና ተሸከሚት ጉብቶ ሶፋ ላይ ካስቀመጣት በኋላ ተመልሶ ይነሳና የቤቱን በር ቆልፎ መሬት ላይ ቁጭ ብሎ ይተነፍሳል)

መሲ

ምን ሆነህ ነው

ዴቭ

ሊንዳ

መሲ

ሊንዳ ምን

ዴቭ

ኧረ ተይኝ እቴ . . . ምን ተብሎ ይነገራል ብቻ ተከድኖ ይብሰል ሆ!

ሲን 19

ውጪ እናኑ በር ጋር ቀን

(ሜላትና እናኑ ሲጫወቱ ቆይተው እናኑ ሜላትን እየሸኘቻት መኪና መጥቶ ይቆማል)

ጂሚ

ይቅርታ የኔ እናት ደህና አመሹ

እናኑ

እግዜር ይመስገን እርሶስ እንደምን አመሹ

ጂሚ

ዴቭ እዚ ግቢ ነው የሚኖረው ብለውኝ ነበር

እናኑ

ዳዊትን ነው

ጂሚ

ያ! ዴቭን ነው

እናኑ

አዩ ለቋል እኮ ለእርሶም አልነገሮትም አከስቱ ኖት

ጂሚ

ኖ ፍቅረኛዬ ነበር ዴቮ ማ ላቭ ለምን እንደዚህ ማድረግ አስፈለገ (መሪውን ትደበድባለች)

ሜላት

(እንዲህ አይነት የወረደ ስብዕና ያለው ወንድ በማፍቀሯ ስሜቷ ይጎዳል)

እናኑ

ምን አሉ አንቱ ፍቅረኛዬ

ጂሚ

አዎ በጣም ጣፋጭ የፍቅር ጊዜያትን አሳልፈን ነበር ግን በስተመጨረሻ ከዳኝ መሰለኝ እኔኮ በፍቅሩ እፍ ክንፍ ብዬለታለው

እናኑ

አንቺ ቅሌታም አሮጊት የልጅ ልጅሽን በምትድሪበት ዕድሜሽ ካንድ ፍሬ ልጅ ፍቅር ያዘኝ ስትይ አታፍሪም . . ነይ ውረጅ አሁን ስጋሽን ነው የምዘለዝልልሽ

ጂሚ

(መኪናዋን ሎክ ታደርገዋለች) ኦ ሴኩሪቲ የኔ እህት በኋላ ከአሜሪካ መንግስት ጋር ነው ፀብሽ እኔ ተናግሬያለው (መኪናዋን አስነስታ ትነዳዋለች)

እናኑ

ነይ ውረጅ እኮ ነው የምልሽ (መኪናውን እየተከተለች ትንሽ ትሮጥና ደክሟት ትቆማለች) ኣይ ዘም ሰው ረከሰ! (ትሄድና ሜላትን ታባብላታለች) ኣይዞሽ ሜላትዬ እንግዲህ ምን አደርገዋለው ጣት በሰበሰ ተብሎ ተቆርጦ አይጣል

ሲን 20

ውስጥ መሲ ቤት ምሽት

(ዴቭ እና መሲ ምግብ ቀርቦ እየበሉ ይታያል)

ዴቭ

(ጠቅለል አድርጎ ለመጉረስ እየተሰናዳ) እስኪ ሙያሽ ይቀመስልሽ (ሲጎርስ ጣቱን ይነክሰውና ይጮሀል)

መሲ

(እጁን ታይለታለች) ኣይዞህ ዴቭዬ

ዴቭ

(በቁጣ) ደሞ አይዞህ አትበይኝ ሆን ብለሽና አስበሽበት ነው . . . (በፈገግታ) እንዲህ አይነት ጣፋጭና ጣት የሚያስቆረጥም ምግብ ማን ስሪ አለሽ

መሲ

(አኩርፋ ትቀመጣለች)

ዴቭ

ኧረ መሲ ኣታምርሪ ቀልድ እኮ ነው

መሲ

እንዲህ አይነት ቀልድ አልፈልግም ተቆጣኧኝ እኮ

ዴቭ

እሺ ይቅርታ (ያጎርሳታል)

መሲ

(ምግቡን ሳታላምጥ አፏ ውስጥ ይዛ በሀሳብ ትዋጣለች)

ዴቭ

መሲ አንቺ መሲ መሰረት...

ምልሰት 10 አመት ወደ ኋላ

ሲን 21

ውስጥ የመሲ አባት አቶ ተሾመ መኖሪያ ቤት

(የመሲ ድምፅ እንደ አስፈላጊነቱ ምስሉ ላይ ተደርቦ ሊደመጥ ይችላል)

አቶ ተሾመ

(በተመስጦ መፅሀፍ ያነባሉ)

መሲ

(እየጠቀለለች አባቷን ታነርሳለች)

አቶ ተሾመ

እየበላሽ ለራስሽም እየበላሽ

(ከመፅሀፉ ላይ ዓይናቸውን ሳይነቅሉ እየጎረሱ ምግቡ ያልቃል ጉርሻውም ይቆማል)

ጠግበሽ በላሽ

(አንገታቸውን ለአፍታ ወደ መሲ ያዞራሉ)

መሲ

(የሚያምረው ፈገግታዋ እህል በአፏ እንዳልዞረ የሚያሳብቀው ከንፈሯን አልፎ ይታያል)

አቶ ተሾመ

አልበላሽም ኢይደል

መሲ

በልቻለው አባቢዬ

አቶ ተሾመ

(መፅሀፋቸውን ያስቀምጡና ቀበቷቸውን ይፈታሉ)

መሲ

አባብዬ ስሞትልህ...

አቶ ተሾመ

(እየገረፏት)

ለራስሽ በደምብ እየበላሽ አላልኩም ... አላልኩም ወይ

መሲ

ብለሀል አባብዬ

አቶ ተሾመ

እናስ

መሲ

በልቻለው እኮ አባቢዬ ስላላየኸኝ ነው

አቶ ተሾመ

ዝም በይ አንቺ ቀጣፊ ዋሾ!

ወደ ቀደመው ትዕይንት

ሲን 22

ውስጥ መሲ ቤት ምሽት

ዴቭ

(እራሱን በግርምት እየነቀነቀ)

በጣም የምትገርሚ ልጅ ነሽ

መሲ

(ዕንባዋን እየጠረገች)

እየበላህ

ዴቭ

አይ በቃኝ በላው

መሲ

አስደበርኩህ አይደል

ዴቭ

ኧረ በፍጹም በቃ ወደ ቤት ልሂድ ለግብጥው አመሰግናለው

መሲ

እንካ ይሄን መፅሀፍ እንቅልፍህ እስኪወስድህ አንብበው

ዴቭ

እሺ

(ተቀብሏት ይወጣል)

ሲን 23

ውጪ ግቢ ውስጥ ምሽት

ያሚ

(ከስራ መልስ ወደግቢ ስትገባ ዴቭ ከመሲ ቤት ሲወጣ ታየዋለች)

ተይዘሀል!

ዴቭ

(ይደነግጣል)

አንቺ ኮቴ የለሽም እንዴ

ያሚ

ከየት ይመጣል ብለህ ነው በመንገድ አልቋል . . . በዚ ሰዓት ከመሲ ቤት እንዴት ነው

ዴቭ

እ.... መደበሪያ ነገር መፅሀፍ ልቀበላት መጥቼ

ያሚ

አይ ጥሩ ነው ብቻ እንኳንም ከሊንዳ ቤት አልሆነ

ዴቭ

ነገረኛ! ይልቅ ጨረቃዋ ደስ ትላለች . . . ካልደከመሽ ደጅ ላይ ትንሽ እናምሽ

ያሚ

እም... እሺ ልብሴን ቀይሬ መጣው

ዴቭ

(ደጅ ላይ ቁጭ ብሎ ይጠብቃታል)

ያሚ

(ቱታ ለብሳ ከላይ ትከሻዋ ላይ ፎጣ ጣል አድርጋ ከዴቭ ትንሽ ራቅ ብላ ትቀመጣለች)

ዴቭ

እሺ ውሎ እንዴት ነበር

ያሚ

መዋሸት ይቻላል

ዴቭ

በፍፁም ያውም በጨረቃ ፊት

ያሚ

(ቀና ብላ ጨረቃን ታያትና)

ምነው ባላወራው ከምል ድብቅነቱ አይሻልም

ዴቭ

ግድየለሽም ለኔ ከነገርሽኝ አትይም

ያሚ

እንዴት ላምንህ እችላለው

ዴቭ

ጨረቃ ዋስ ትሁነኝ

ያሚ

(አሁንም ቀና ብላ ጨረቃዋን ታይና ፈገግ ትላለች)

ያው ተራ ሴት ነኝ . . የወረደ ስብዕና ያላት ተራሴት . . በየውስኪ ቤቱ በብራቸው ከሚያስቡ ሰዎች ጎን የማልጠፋ ተራ ሴት . . በጥረቴ አፈራሁት የምለው ካልሲ እንኳን የሌለኝ ተራ ሴት . . አሁን ግን ሁሉም ነገር አስጠላኝ

ዴቭ

ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ የእስከዛሬ ህይወትሽን ጠላሽው

ያሚ

ውስጤ ንፁህ ልቡን የምከተለው የኔ የምለው ሰው ፈለገ

(ትንሽ ፀጥታ ይሰፍናል)

ዴቭ

(የራሱ ህይወት ትዝ ይለውና ትንሽ ከቆዘመ በኋላ ወደ ያሚ ጠጋ ብሎ ይቀመጣል)

እኔን ብቻ ነው የሚበርደኝ

ያሚ

(ፎጣውን አብሯት እንዲለብስ ትጋብዘዋለች)

ዴቭ

(ፎጣውን ይለብስና ወደ እሷ ሲዞር አይን ለአይን ይገጣጠማሉ)

ያሚ

(አይኗን ጨፍና በተመስጦ መተንፈስ ትጀምራለች)

ዴቭ

(ከንፈሯን ይስማታል)

ውስጥ መሲ ቤት

መሲ

(ቤት ውስጥ ሆና በመስኮት ታያቸውና)

የለሊት ወፍ አይጥ ነሽ ሲሏት «እዩት ክንፌን» ወፍ ነሽ ሲሏት «እዩት ጥርሴን» አለች አሉ ...አንት ሁለት ቤት አዳሪ !

ሲን 24

ውስጥ ያሚ መኝታ ክፍል ምሽት

ያሚ

(አልጋዋ ላይ ቁጭ ብላ በቀደመው ትዕይንት የነበረችበትን ደስ የሚል የፍቅር ድባብ እያስታወሰች ብቻዋን ፈገግ ትላለች)

ሲን 25

ውስጥ ዴቭ ቤት ምሽት

ዴቭ

(ቤት ሲቀይር ያጠፋውን ስልኩን ሲያበራው በርከት ያሉ ያልተሳካ ጥሪና የጽሁፍ መልዕክቶች በተከታታይ እየገቡ እዛው ላይ ስልኩ ይጠራል)

ሜላት

ሄሎ ዴቭ አንተ ዴቭ

ዴቭ

ወዬ ሜላትዬ

ሜላት

ዴቭዬ ናፍቀኸኛል ለምንድው እንደዚህ የጠፋህብኝ ዴቭዬ አስጠላሁህ እንዴ

ዴቭ

የኔ ማር አንቺ ደሞ ምንሽ ይጠላል በጣም ከባድ ችግር ላይ ሆኜ ነው

ሜላት

እኔን ይቸግረኝ የኔ አባት ምነው ምን አገኘብኝ

ዴቭ

አይ ይቅር ሜላትዬ የኔው ይበቃል አንቺ እንድትጨነቂብኝ አልፈልግም ይልቅ ብዙ ነገሮች ናፍቀውኛል

ሜላት

እንዴት አስቻለህ ግን . . ዴቭ ሙት በጣም ጨካኝ ነህ

ዴቭ

ምን ላድርግ ሜላትዬ ካንቺ ናፍቆት በላይ የሚያስጨንቅ ችግር ባይገጥመኝ.... (ከደቂቃዎች በፊት የያሚን ከንፈር በቀመሰበት ምላሱ ሌላ ሴት እየደለለበት መሆኑ ከብዶት ውሸቱን እንደ ጉሽ ጠላ ገፈት እንትፍ እያለ ስልኩን ከጆሮው አንስቶ ይዘጋዋል) አቤት! አቤት! ኧረ የኔስ በዛ ቢያንስ የዚች ቆንጆ ከንፈር ጣዕም ትንሽ እንኳን ከምላሴ እስኪጠፋ ብጠብቅ ምን አለበት ይሄስ ልከፍት ነው እንጂ በጤናማ አይመስለኝም (ስልኩን አስቀምጦ ወደ መኝታው ይሄዳል)

ሲን 26

ውጪ ግቢ ውስጥ እኩለ ለሊት

ሊንዳ

(ሰክራ ወደ ግቢው እየተንገዳገደችና እየዘፈነች ትገባለች)

የወንዜ ልጅ ያውም የዓባይ

አቤት አቋም አወይ ፀባይ

ኡኡኡይ.... ማን እንደ ሀበሻ ወንድ የሀገሬ ወንዶች እወዳችኋለው! ኑሩልኝ! አሁን የሌላ ሀገር ወንድም ወንድ ሊባል በፍፁም . . .(ወደ ዴቭ ቤት ትሄዳለች) ሀቢቢዬ.... ሀቢብ.... (በሩን ትደበድባለች)

ዴቭ

(ሊከፍትላት ይነሳና መዘዙን ፈርቶ ተመልሶ እንዳልሰማ ሆኖ ይተኛል)

ሊንዳ

ኤጭ! እቺ ሀቢቢ ደሞ ምላስ ብቻ ነች ምላስ ብቻውን ምን ያደርጋል ተግባር ያስፈልጋል አው የተግባር ፈተናውን ካላለፍክ ማንም መንጃፍቃድ አይሰጥህም::

(እየተንገዳገደች ወደ ቤቷ ትሄዳለች)

የወንዜ ልጅ ያውም የዓባይ

አቤት አቋም አቤት ፀባይ

ሲን 27

ውስጥ ዴቭ ቤት ጠዋት

ዴቭ

(ከስፖርት መልስ ቱታውን እንደለበሰ የተነጠፈው አልጋ ላይ ጋደም ብሎ ሙዚቃ ይሰማል)

ውጪ

ያሚ

(ወደ ስራ ለመሄድ አምሮባት ሽቅርቅር ብላ የዴቭን ቤት እያየች አልፋ ልትሄድ ትልና አመንትታ ትመለሳለች)

ውስጥ ዴቭ ቤት

ያሚ

እዚ ቤት እንደምን አደራቹ (አንገቷን አስገብታ ትቆማለች) መግባት ይቻላል

ዴቭ

እንዴ ችግር አንተ ችግር ና እንጂ ወዴት እየሄድክ ነው ልክ አሁን አንቺ በበር ስትገቢ ችግሬ በመስኮት ወጣ

ያሚ

ኧረ ሀንድ ፊልም ዘፈኑ ብቻ ነው የቀረህ

ዴቭ

ሀጃህ ሀቴ ቱማቱጂሴ ገልቢ ሙጀራ....

ያሚ

(ፈገግታ) ደህና አደርክልኝ

ዴቭ

እ... ምን አልሽኝ

ያሚ

ደህና አደርክ ወይ

ዴቭ

እ.... እኔ ደግሞ ደህና አደርክልኝ ያልሽ መስሎኝ

ያሚ

(ፈገግታ) ማታ ሊንዳ ረበሸችህ አይደል

ዴቭ

ምን ሊንዳ መጥታ ነበር ተበላሽተህል አትይኝም (ሱሪውን ከፍ አድርጎ ያያል)

ያሚ

በል ደህና ዋል ቁጭ ብዬ ቀልድህን ከሰማው ስራ መፍታቴ ነው

ዴቭ

(እጇን ይይዛታል)

ልትሄጂ ነው

ያሚ

አዎ ዴቭዬ መልካም ቀን የኔ ቆንጆ

ዴቭ

(እጇን ይስማታል)

ያሚ

(ደስ እያላት ከቤት ትወጣለች)

ዴቭ

አቦ ይቺ ልጅ ፍቅር ልታሲዘኝ ነው! ፍቅቅቅቅር (ብሎ ይጮሀል)

ያሚ

(እሷ የጠራት መስሏት በሩን ከፍታ አንገቷን እያስገባች) ወዬ የኔ ውድ

ዴቭ

ላንቺም መልካም ቀን!

ሞንታጅ ሲኖች

በተለያየ ቀን እየሳመችው ወደ ሰራ ስትሄድ አንድ ቀን አልጋው ላይ አጥታው ግራ ሲገባት ከጓላዋ ተደብቆ ሲያስደነግጣት

ግቢ ውስጥ ስፖርት አብረው ሲሰሩ ደረትና ጀርባዋን ይዞ ቀጥ ሲያደርጋት

ሊንዳ ሰክራ መጥታ የዴቭን ቤት ስትደበድብ ያሚ ስትከፍትላት

ወደ ሰራ አብረው እየተሳሳቁ ሲወጡ ሊንዳ እየገላመጠች ስትመለከታቸው ያሚ ሊንዳን ለማስቀናት ዴቭን አሰቁማ ስትሰመው

ዴቭ

እንጣአሰይ አወይ ከንፈርሽ ሲጥም ምን አርገሽበት ነው

ያሚ

(ሊንዳን ለማናደድ ከት ብላ እየሳቀች) እኔንጃ ጨው ነው መሰለኝ

ሊንዳ

(በቅናት ትንጨረጨራለች) ኢናል ዐመከ ነአል ጡዝጡዝ

እሁድ ቀን ዴቭ ቤት አልጋ ላይ ተያይዘው እየዘለሉ ሲጨፍሩ ሲወድቁና ሲመሳሰጡ

ያሚ ተኝታ ዴቭ ስሟት ወደ ሰራ ሲሄድ

ያሚ መሲ ቤት ውስጥ ቡና ማፍላት እየለመደች ሲገነፍልባት

ያሚ

ወይኔ ጉዴ ጀበናው ቮሚት አለው

ያሚ ከመሲ ጋር ቁጭ ብላ እያዛጋት መፅሀፍ ስታነብ ከዛም ቤት ላንብበው ብላ ስትወጣ

ያሚ ቤት ውስጥ የመፅሀፉን መጀመሪያ አለፍ ብላ መሀከለኛውን ክፍል ከዛም ማገባደጃውን አንብባ ወደ መሲ ቤት ስትሄድ

ያሚ

ዋው እንዴት ደስ የሚል ታሪክ ነው በናትሽ መፅሀፍ ማንበብ እንድወድ ነው ያደረገኝ ፕሊስ ሌላም እንዲህ አይነት መፅሀፍ ካለሽ

መሲ

ኧረ አለኝ ከዛ በፊት እዚ መፅሀፍ ላይ ያነበብሽውን ነገር አንድ በአንድ እንድትነግሪኝ እፈልጋለው

ያሚ

መጀመሪያ ማሳደጊያ ውስጥ አብረው ነው ያደጉት ከዛ እሱ ዕድሜው ደርሶ ቀድሟት ይወጣና ድሬዳዋ ሄዶ ንግድ ስራ ይጀምራል የምታፈቅረው ልጅ ደግሞ እሷም ዕድሜዋ ደርሶ ከማሳደጊያ ስትወጣ አድራሻውን ብታፈላልግ ታጣዋለች መጨረሻላይ ግን ድሬዳዋ ነው ሲባል ሰምታ ሄዳ ታገኘውና አብረው ይኖራሉ፡፡ በቃ በጣም ደስ ይላል ወይ ፍቅር!

መሲ

ምዕራፍ አንድ ምዕራፍ አራት ምዕራፍ ዘጠኝ

ያሚ

ምንድን ነው እሱ

መሲ

ገረፍ ገረፍ እያደረግሽ ያነበብሻቸው ምዕራፎች

ያሚ

ምዕራፍ ሰባትንም ግን ትንሽ ትንሽ አንብቤዋለው መሲዬ ሙች

ሲን 28

ውስጥ እናኑ ግቢ ቀን

እናኑ

(ልብስ እያጠበች ዴቭ ወደ ግቢው ሲገባ ትመለከታለች)

ውጣልኝ ብያለው በህግ አምላክ ሰውዬ ፖሊስ ጠርቼ ሳላስቀፈድድህ ውጣ!

ዴቭ

ማሚዬ እናቴ (ዝቅ ብሎ ጉልበቷን እየያዘ) ይቅር በይኝ እናቴ ሴቶቹ እንዳያገኙኝ ብዬ ነው የጠፋሁት

እናኑ

ተነስ ከእግሬ ላይ ብዬሀለው ከእጇ እንዳልበላህ እንዳልጠጣህ ሄጃለው እንኳን ሳትለኝ ውልቅ ብለህ ትወጣለህ ነገሩ ባዳ ምን ጊዜም ባዳ ነው

ዴቭ

ተይ እንጂ ማሚዬ እኔን ባዳ (ያቅፋታል)

እናኑ

(አንጀቷ አልችል ብሎ በአረፋ እጇ አንገቱን ይዛ እያገላበጠች ትስመዋለች)

ደሞ እኮ ከስቷል እሺ ለመሆኑ ምግብ የሚሰራልህ አለ

ዴቭ

ከየት ይመጣል

እናኑ

እኔ አፈር ልብላ ሂድ ግባ ወደቤት እጇን ተለቃልቄ እመጣለው

ዴቭ

(ወደ ቤት ይገባል)

እናኑ

(ዴቭ መግባቱን ታይና በጥድፊያ ስልኳን አውጥታ ሜላት ጋር ትደውላለች)

ሄሎ ልጄ . . ዳዊት መጥቷል ቶሎ ድረሽ . . ደሞ እሷ ነገረችኝ እንዳትይ ችግር የለውም አይሄድም እኔ አቆይልሻለው

(ስልኩን ደረቷ ውስጥ ከታ ወደ ቤት ትገባለች)

ሲን 29

ውስጥ እናኑ ቤት ቀን

ዴቭ

(ምግብ ቀርቦለት በጥድፊያ ሲበላ ይታያል)

እናኑ

ኧረ ልጄ ቀስ በል

ዴቭ

እጅሽ እንዴት እንደናፈቀኝ አላወቅሽም

እናኑ

አዬ... ተወኝ እስኪ ይኸው እጋግረዋለው መሶብ ሙሉ ይሻግታል የወላድ መካን ማለት እንደኔ ነው ያውም የባዕድ ገረድ ለመሆን ልጆቿ የከዱት . . .

ዴቭ

(መብላቱን ያቆማል)

እናኑ

(ማልቀስ ትጀምራለች) ቤት ሙሉ ልጅ ወልጄ በስተርጅና ባዶዬን ያስቀረኝ ፈጣሪዬን ምን አድርጌው ይሆን

ዴቭ

ተያ ማሚ ደሞ እኔ አለሁልሽ አይደል እንዴ ለምንድን ነው ፈጣሪን የምታማርሪው

እናኑ

እኔማ እንደ እናት አከብረህ ስትታዘዘኝ . . የሴት ቤት ነው ተብሎ እንዳልናቅ መከታ ስትሆነኝ . . ፈጣሪ ባንተ ካሰኝ ብዬ ነበር እህህ... እማዬ እያልክ አታለልከኝ አንት አፈ ቂቤ

ዴቭ

ማሚዬ አብሬሽ መሆኑን ካንቺ ይልቅ እንደምፈልገው ታውቂያለሽ . . ግን ደግሞ አንቺን ማንም ሰው በክፉ እንዳያይብኝ እያልኩ መልሼ ራሴው ስምሽን ካስጠፋሁት ምን ዋጋ አለው በቃ ትንሽ ጊዜ ባህሪዬን ላስተካክልና እመለሳለው

እናኑ

መች ነው የምትመለሰው

ዴቭ

ለኔ የምትሆነኝ ሴት አገኘው ስል አንቺ ጋር አመጣትና ከወደድሽልኝ መርቀሽን ተሰብስቤ አብሬሽ እኖራለው አለበለዚያ ግን በተከበርሽበት ሰፈር አስር ሴት ግቢ ውስጥ እያመላለስኩ ስምሽን ማስጠፋት አልፈልግም

እናኑ

ሜላትን የመሰለች ዕንቁ እምቢ ብለህ ላንተ የምትሆንህን ከየት ነው የምታመጣው

ዴቭ

ማሚ ደግሞ አሁን ለሜላት አይነት የምታሳሳ ሴት የኔ አይነት ወንድ ይገባታል

ሜላት

(ከውጪ ጉብታ እየሰማች እንደነበር ምስሉ ላይ ስናይ እንቆይና ማውራት ትጀምራለች)

(ዕንባ እየተናነቃት) እንኳን እሺ

ታዲያ መጀመሪያ አርፈህ አትቀመጥም ነበር ስንት ነገር ካስለመድከኝ በኋላ ነው እንዲህ የምትለው

ዴቭ

(ዝም ብሎ ተነስቶ ይሄዳል)

ሜላት

(መንገድ ትዘጋበታለች)

መልስልኛ አብረኸኝ የማትሆን ከሆነ ለምን እንዳፈቅርህ አደረከኝ

ዴቭ

እንዲህ ነው ልልሽ አልችልም ምክንያቱም አንዳንድ መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አሉ

(ትቷት ይሄዳል)

ሜላት

(እያለቀሰች) እናንዬ ጥሎኝ ሄደ እኮ

እናኑ

(አቅፋ ታባብላታለች) እስኪ ጠንከር በይ በትንሽ ትልቁ ስሜትሽ አይጎዳ

ሲን 30

ውስጥ መሲ ቤት ቀን

መሲ

(ያሚን የሀገር ባህል ልብስ እያለበሰቻት ይታያል)

በለው እንዴት እንዳማረብሽ

ያሚ

መሲዬ ግን እንዲህ አይነት አለባበስ ይስበዋል ብለሽ ነው

መሲ

በምን እንደምትስቢው ደሞ ሌላ መላ አለ

ያሚ

መሲ . . . አንቺም ዴቭን ትወጂዋለሽ አይደል

መሲ

አልደብቅሽም (ልትናገር የነበረውን ትተወውና) ምንም ለሱ ስሜት የለኝም

ያሚ

የእውነት

መሲ

አው (ከሙዳይ ውስጥ እንዝርት አውጥታ ትሰጣታለች)

ያሚ

እንጨት ደግሞ ምን ያደርግልኛል

መሲ

እንዝርት ነው የሚባለው የድሮ እናቶቻችን

ሲን 3ነ

ውስጥ ዴቭ ቤት ቀን

(በዕጣን የታጀበው የቡና ድባብ ካሜራው ያስመለከታል)

ዴቭ

(በሩን ከፍቶ ሲገባ ያየው ነገር የፊቱን ገፅታ በግምት ይመላዋል)

ያሚ

(የሀገር ባህል ልብሷን ለብሳ ቡናውን ስታፈላ ይታያል)

ዴቭ

እንዴ ያሚዬ

ያሚ

(ተነስታ ትስመዋለች) እንኳን ደህና መጣህ ባሌ

ዴቭ

ምን ምን እስኪ ድገሚልኝ

ያሚ

እንኳን ደህና መጣህ ባሌ

ዴቭ

ተዉ ተዉ ግን ይሄን ሳይጋቡ ባሌ ሚስቴ

ያሚ

ምነው እንደምንሆን ትጠራጠራለህ እንዴ

ዴቭ

(ፈንዲሻ እየዘገነ) ባልፈራውም ባሌ ሚስቴን በጉጉት እየጠበቅን እስከዛው ውዴ ፍቅሬ ብንባባል ጥሩ አይመስልሽም

ያሚ

እሺ ውዴ ፍቅሬ! እንዳልክ . . . ቡና እስኪፈላ ትንሽዬ ስራ ልስራ (ከሙዳይ ውስጥ እንዝርት ታወጣና ቀሚሷን እስከጭኗ ድረስ በዝግታ ወደ ላይ ትሰበስበዋለች)

ዴቭ

(ቀልቡ ወደ ጭኗ ይሰረቃል)

ያሚ

(የዴቭ ቀልብ ወደ እሷ መሆኑን በነን ተመልክታ ካረጋገጠች በኋላ) የማትችለውን እንዝርት ፈተላ ለዓመል ያህል ባቷ ላይ ታመላልሰዋለች

ዴቭ

(በስሜት ማዕበል ይንሳፈፋል)

ሊንዳ

(ባቷን ያጋለጠ አለባበስ ለብሳ በሰሀን ገንፎ ይዛ ትገባለች)

ቆንጆ ገንፎ ሰርቼልህ መጣው ዴቭዬ

ዴቭ

(ሊንዳ ባት ላይ ዓይኑ እንደተተከለ ሊቆጣት ይሞክራል)

ምን ሆነሽ ነው ትልቅ ሰው አይደለሽ እንዴ ሰው ቤት ዘው ተብሎ ይገባል በይ አሁን ገንፎሽን አስቀምጪና ውጪ

ሊንዳ

(ከት ብላ ስቃ) ወይ ሀቢቢዬ ዳሌዬን ተመስጦ እየሾፈ ውጪ አላለኝም ያሚዬ

ያሚ

ስሜን አትጥሪ!(ታንቧርቅባታለች)

ሊንዳ

ኧረ ቀስ! የሌለሽን ጭን ገልጠሽ እያሳየሽ ስለመጣሁብሽ በጣም ተንዘረዘርሽ የሆንሽ ማማሰያ አቋም

ያሚ

ምን አልሽ አንቺ የገረጀፍሽ

ዴቭ

(ተዉ በማለት ፈንታ ሳቁ ያፍነዋል)

ሊንዳ

ማ! እኔ የምቀኛ ወሬ አልሰማም እሺ

ያሚ

የሆንሽ ክብረ ቢስ

ሊንዳ

የኛ ባለ ክብር የሆንሽ የብር አስር ነገር

ዴቭ

ኧረ ተዉ ባካቹ

ያሚ

ካንቺ ጋር ትርፍ ንግግር አልፈልግም ዛሬውኑ ይሄን ግቢ ለቀሽ እንድትወጪ

ሊንዳ

ማነው የሚያስወጣኝ አንቺ! ምነው ቅምጥ መሆንሽን ንገሩኝ አልሽ ስሚ ያንቺ አይነት 30 ቅምጥ እየመጣ ሄዷል ማንም ግንውጡ ብሎን አያውቅም እሺ! እኛ እኮ ከባለቤቱ ጋር ህጋዊ ውል ያለን ተከራዮች ነን እንዳንቺ ውጡ ስንባል የምንወጣ ነአል ጡዝጡዝ ዐመክ መሰልንሽ

ያሚ

አናትሽን ነው በዚህ ጀበና የምከፍልልሽ

ዴቭ

(እጇን ይይዛትና ጀበናውን በትግል ይቀበላታል)

መሲ

(ጭቅጭቁን ሰምታ መፅሀፏን እንደያዘች ትመጣና በዚያ ቀውጢ የሴቶች ፀብ ውስጥ ከያዘችው መፅሀፉ ስለግጭት አፈታት ዘይቤዎች ነ.2.3 እያለች ትዘረዝራለች)

ዴቭ

(አንድ ጊዜ ወደ ያሚ መልክ አንዴም ወደ ሊንዳ ዳሌ እየጠቆመ)

ኧረ ተዉ ባካቹ!

ሊንዳ

(ከመሲ እጅ ላይ በንዴት መፅሀፉን ነጥቃ ወደ ያሚ ትወርውረዋለች)

መሲ

(በንዴት ፊቷ ልውጥውጥ ይልና ሊንዳን በጥፊ ትደረግማታለች ስክሪን ይጨልማል)

ሲን 32

ውጪ መኪና ውስጥ ቀን

ተካበ

(መኪና እየነዳ ስልኩ ይጠራል መንገዱን አየት አየት አድርጎ ያነሳዋል)

ወዬ ያሚዬ

ያሚ

ዛሬውኑ ላገኝህ እፈልጋለው

ተካበ

እንደው የኔ እመቤት እባክሽ ለነገ ታደርጊልኝ

ያሚ

አልችልም!

ተካበ

ዝጊ ወደዛ! ስሚ በፈለኩት ደቂቃና ሰከንድ ልጠራሽም ሂጅ ልልሽም ስልጣን ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ ተግባባን (ስልኩን ዘግቶ ይወረውረዋል)

ሲን 33

ውጪ ግቢ ውስጥ ቀን

ያሚ

(ዴቭ በር ላይ ጨረቃ ምስክር ትሁነኝ ያለበት ቦታ ተቀምጣ በሩን ታንኳኳለች)

ዴቭ

ያሚዬ . . ምነው ውስጥ አትገቢም እንዴ

ያሚ

አይ እዚ ጋር እንድናወራ ነው የምፈልገው

ዴቭ

(አጠገቧ ይቀመጣል)

ያሚ

በጨረቃ የነገርከኝኝን በፀሀይ እንድትደግምልኝ እፈልጋለው የምር ትወደኛለህ ግን

ዴቭ

ፀሀይ ምስክር ትሁነኝ በጣም ነው የምወድሽ

ያሚ

ያንተ ብቻ መሆን እፈልጋለው አንተስ የኔ ብቻ ለመሆን ዝግጁ ነህ

መሲ

(ከውጪ ትገባና በሩን ልትዘጋው ስትል የተካበን መኪና ሲመጣ ታየዋለች ከዛም ለያሚ ተካበ መምጣቱን ነግራ ወደ ቤት ትገባለች)

ያሚ

(ትደነጋገራለች)

ወይኔ ጉዴ በቃ በኋላ እመጣለው (እየሮጠች ወደ ቤት ትገባለች)

ተካበ

(ወደ ግቢ ይገባና ዴቭ ጋር ደርሶ ይቆማል) ስማ! ቀንህ ደርሷል ቤት ፈልግና በፍጥነት ከዚህ ግቢ ውልቅ በል ኋላ አንድ ቀን አሳልፋለው በልና ውርድ ከራሴ! (ገላምጦት ወደ ያሚ ቤት ይገባል)

ዴቭ

(አንገቱን አቀርቅሮ ንዴቱን ውጦ ዝም ይላል)

ሲን 34

ውስጥ ያሚ ቤት ቀን

ተካበ

(ይገባና በቁጣ ንግግሩን ይጀምራል) ስሚ! ምንድን ነው እንዲህ ሰው የምታንገበግቢው

ያሚ

ተኪ....(ተነስታ ትጠመጠምበትና ትደባብሰዋለች)

ተካበ

(ቁጣው ወደ ሳቅና የመማለል ስሜት እየተቀየረ) አንቺ ደሞ እስኪ ትንሽ ልቆጣሽ ምንድን ነው እንዲህ ሰው ማንገብገብ

ሲን 35

ውጪ ግቢ ውስጥ ቀን

ዴቭ

(እዛው ያለበት ቦታ ተቀምጦ ሳቅና ልፊያ ይሰማዋል)

ሲን 36

ውስጥ መሲ ቤት ቀን

መሲ

(ከህደት ሊገልፅ የሚችል ርዕስ ሽፋኑ ላይ በጉልህ የሚታይ መፅሀፍ ለማንበብ ተመቻችታ ተቀምጣ ካሴት ስትከፍት ለስለስ ያለ ሙዚቃ ይደመጣል)

ብወድሽ ነው እንጂ የማነክሰው

እኔ ራሴን ችዬ ቆሜ የምሄድ ሰው

ምነው ብታስጠሪኝ እኔን አስታውሰሽ

እደጅ ቁጭ ብዬ እቤቴ ሳመሽ

ሲን 37

ውጪ ግቢ ውስጥ ቀን

በር ይንኳኳል

ዬቭ

(የግቢውን በር ይከፍታል)

ሜላት

(በፍርሀት ፊቷን አዙራ ትቃኛለች)

ተካበ

ሜላት! (ወደ ውጪ ወጥቶ በሩን ይዘጋዋል)

ሲን 38

ውስጥ ያሚ ቤት ሳሎን

(ያሚ ከተካበ ጋር ሶፋ ላይ ተቀራርበው ተቀምጠው ይታያሉ)

ተካበ

(ሊስማት ይጠጋል)

ያሚ

(ወደ ኋላ ሸሸት እያለች) ቆይ ከዛ በፊት እንድታደርግልኝ የምፈልገው ነገር አለ

ተካበ

በዚ ሰዓት ሌላ አይነት ፍላጎት

ያሚ

(ታኮርፋለች)

ተካበ

እሺ ምንድንነው

ያሚ

ሊንዳን ከዚ ግቢ እንድታስወጣልኝ እፈልጋለው ዛሬውኑ

ተካበ

ውይ ለዚች ነው አሁኑኑ ነው የማስወጣልሽ

(ይወጣል ካሜራ ተከትሎት ወደ ሊንዳ ቤት)

ሲን 39

ውጪ ሊንዳ ቤት በር ላይ ቀን

(በር ይንኳኳል)

ሊንዳ

(ስትከፍት አከራይዋ ተካበን ታየዋለች)

ተኪዬ. እንዴት ነህልኝ የኔ ጌታ

ተካበ

እኔ የምልሽ

ሊንዳ

(ከንፈሯን በስሱ ነክሳ በአይኗ እያሽኮረመመችው)

እ አንተ የምትለኝ

ተካበ

(ወደ ያሚ ቤትና ወደ መሲ ቤት ደጅ ላይ ሰው አለመኖሩን እየቃኘ)

እ.. እኔ የምልሽ

ሊንዳ

(ገባ ብለህ ብትለኝ አይሻልም)

ተካበ

(ግራ ቀኝ ቃኝቶ ይገባል)

ሲን 41

ውስጥ ያሚ ቤት ቀን

ያሚ

(ብቻዋን በንዴት ትቁነጠነጣለች)

ተካበ

(ከውጪ ይገባል የሸሚዙ አቆላለፍ ተዛንፏል ፀጉሩ ተፈላልሷል)

ያሚ

እስካሁን ምን እየሰራህ ነበር

ተካበ

ቤት እንድትለቅ ንገራት አላልሽኝም

ያሚ

(ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ፀጉሩ አተኩራ ትመለከተውና)

ምን ስታረጉ ነበር

ተካበ

ዝኒ ወደዛ! (በጥፊ ይመታታል) ምንስ ባደርግ

(ከጠረጴዛው ላይ የመኪናውን ቁልፍ ያነሳና ይወጣል)

ያሚ

(እንደ መቀወስ ያደርጋትና ትጮህለች)

ዋይ...

ሊንዳ

(በር ጋር ቆማ ታሰናብተዋለች)

ሲን 42

ውጪ ቡልቡላ ሰስፔንሽን ድልድዩ ስር ወንዙ ዳር ቀን

ሜላት

ዴቭዬ ምን ሆነህ ነው የኔ አባት እባክህ እንዲህ አትከፋ የኔጌታ አንተ እኮ ስቀህ ስታስቅ ነው የሚያምርብህ

ዴቭ

(አንገቱን በዝግታ ወደ ሜላት አዙሮ አተኩሮ ይመለከታትና) ዛሬ ግን ከፋኝ

ሜላት

(ከቃሉ እኩል አብሮ ዕንባዋ ዱብ ዱብ ይላል) እኔን ይከፋኝ ጌትዬ እኔን ክፍት ይበለኝ (ታቅፈዋለች)

ዴቭ

(ሳያስበው እሱም ያቅፋታል)

ሜላት

(ለቅሶዋን ታቀልጠዋለች)

ዴቭ

በቃ! በቃ! (ዕንባዋን እየጠረገ) አንቺን ምንድን ነው እንዲህ የሚስለቅስሽ

ሜላት

(ደስታዋ ሀዘኗን ሲሸፍነው ዕንባዋ ላይ ሳቅ ሲደረብ ይታያል) እኔንጃ

ዴቭ

እስቲ በደምብ ሳቂ

ሜላት

(ፍልቅልቅ ፍንድቅድቅ ትላለች)

ዴቭ

አው ጎበዝ ልጅ

(ፊቷን ሊረጫት እጁን ወደ ውሀው ይልካል)

ሜላት

ፀጉሬ ይበላሻል ዴቭዬ

ዴቭ

ይበላሻ ለኔ አይደል እንዴ ተሰርተሽ የመጣሽው

(ይረጫታል)

ሜላት

እኔም ልረጭህ እችላለው

ዴቭ

አው

ሜላት

(እሷም ከሱ በባሰ ትረጨውና ትሮጣለች)

ዴቭ

(አባሮ ይይዛትና አቅፎ ውሀ ውስጥ ይነክራታል)

ሲን 43

ውስጥ ተካበ ቤት ምሽት

ሀና

(ሶፋ ላይ ጉልበቷን አቅፋ ተኝታ ይታያል)

ተካበ

(ከውጪ ይገባል) ቅንጥሼ (ሶፋ ላይ መተኛቷን ያያል) አንቺ ቅንጥሼ (ይቀሰቅሳታል) ምን አይነት ስነ ምግባር ነው ገንዘብ አይደል እንዴ እያፈሰስኩበሽ ያለሁት እዛ ሂጂና የምትጋደሚበት ተጋደሚ

ሀና

ምን

ሲን 44

ውጪ የግቢው በር አካባቢ ምሽት

(ዴቭና ሜላት ልብሳቸውና ሰውነታቸው ረጥቦ እየተንቀጠቀጡ ይሄዳሉ)

ዴቭ

አከራዮቼ በጣም አደገኛ ስለሆኑ ቀስ ብለን እንገባና በለሊት ተነስተሽ ውልቅ ትያለሽ ማለት ነው ተግባባን

ሜላት

እሺ ተስማምቻለው

ዴቭ

(የግቢውን በር ይከፍተዋል ከዛም ሜላትን እዛው እንድትቆም አዟት የቤቱን በር ይከፍትና ግቢውን ቃኘት ቃኘት አድርጎ ሜላትን በፍጥነት ወደ ቤቱ ያስገባታል)

ሲን 45

ውስጥ ተካበ ቤት ምሽት

ሀና

(ሻንጣዋን እየነተተች ትወጣና) ስማ እኔ ግን ገንዘብህን ሳይሆን ፍቅርህን ብዬ ነበር እስከዛሬ አብሬ የኖርኩት

ተካበ

አይሆንም ቅንጥሽዬ ብቻዬን ጥለሽኝማ አትሔጂም አንቺ እንደሌሎች ሴቶች ብሬን ሳይሆን እኔን እንደምትፈልጊ አውቃለው እባክሽን ቅንጥሽዬ እባክሽ

ሀና

እስከነ ብርህ ገደል ግባ እሺ! ካሁን ወዲህ እንዲህ አይነት አፀያፊ ቃል እንድትናገረኝ አልፈልግም(ታለቅሳለች)

ሲን 46

ውስጥ ዴቭ ቤት ምሽት

ዴቭ

ታጠቢና ይሄን ቀይሪ

(የራሱን ልብስ ይሰጣታል)

ሜላት

(አንተም ቀይርና አብሬ ከኔ ልብስ ጋር ልጠብልህ)

ዴቭ

እሺ እጠቢና አስቀምጭው አሰጣለው ብለሽ ውጪና አሰጣሻለው!

ሜላት

እሺ አልወጣም

ዴቭ

በቃ መምጣቴን ለአከራዮቼ ሪፖርት ላድርግ

ሜላት

አከራዮችህ ግን ያስጠላሉ ለምንድን ነው እንዲህ የሚስጨንቁህ ቤትህ አይደል እንዴ

ዴቭ

አይ አንቺ! በቃ ሁሉም አከራይ እንደ ማሚ ነው የሚመስልሽ አይደል

ሲን 47

ውስጥ ያሚ ቤት ምሽት

(ቀለል ያለ ግን የተሸቀረቀረ የለሊት ልብስ ለብሳ ወደ ዴቭ ጋር ለመሄድ ተኳኩላ ልትወጣ ስትል በር ላይ ከዴቭ ጋር ይገጣጠማሉ)

ያሚ

ዴቭ ልክ አንተ ጋር ልመጣ ስል

ዴቭ

እ.. አይደል

ያሚ

ፕሊስ ዴቭዬ ለራሴ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ነው በቃ ምንም እንዳትለኝ

ዴቭ

እሺ በቃ ደህና እደሪ

ያሚ

አስጠላውህ አይደል ሲገርም!

ዴቭ

ኧረ እኔ እንደሱ አላልኩም ጨነቀኝ ስላልሽ ነው ልሄድ የነበረው እንጂ ማደርም እችላለው

(ሰፋ ላይ ይቀመጣል)

ያሚ

(ከጀርባው አቅፋው ጉንጯን ጭንቅላቱ ላይ ታስደግፋለች)

አው እንደውም ዛሬ አንተ ዕቅፍ ውስጥ ማንጋት ነው የምፈልገው . . . ደሞ ፀጉርህ እርጥብ ነው ቆይ ላደራርቅልህ

(ወደ መኝታ ክፍሏ ትሄድና ፎጣ ይዛ መጥታ ጸጉሩን እያደራረቀችለት ያወራሉ)

ዴቭዬ ቤት መልቀቅ ይኖርብናል

ዴቭ

አይደል

ያሚ

አው የምከፍልበት ቤት ውስጥ መኖር እፈልጋለው ከዛ ቀጥሎ ደግሞ ትንሽም ብትሆን የራሴን ስራ የመጀመር ሀሳብ አለኝ ምን ይመስልሀል

ዴቭ

ጥሩ ሀሳብ ነው::ግን በስሜታዊነት ሳይሆን ሁሉንም በብስለትና በጊዜው ብታደርጊው መልካም ነው

ያሚ

እኔም እንደዛ ነው የማስበው በአንድ ጀምበር ሁሉን ነገር ልለውጥ አልልም ግን ከዛሬ መጀመር እንዳለብኝ ይሰማኛል ይሄ የኔ ቦታ አይደለም! . . . በቃ እንተኛ

ዴቭ

እሺ (ተነስተው ወደ መኝታ ቤት ይሄዳሉ) ዛሬ ግን ጥሩ ሙድ ላይ ነሽ

ያሚ

ምንም አልልም

ዴቭ

በቃ ዛሬ ልሂድና ነገ አብረን እናድራለን

ያሚ

ይሻላል

ዴቭ

አይመስልሽም

ያሚ

(ትንሽ አሰብ ታርግና ጉንጩን ትስመዋለች) እሺ ደህና እደር በቃ

ዴቭ

(ይወጣል)

ሲን 48

ውስጥ ዴቭ ቤት ምሽት

(ዴቭና ሜላት አልጋ ላይ ተቀምጠው ይታያል)

ሜላት

ዛሬ ደስ የሚል ቀን ነበር

ዴቭ

በቃ እንተኛ በጠዋት መነሳት አለብን

(ጀርባውን ሰጥቷት ይተኛል)

ሜላት

(አቅፋው ትተኛለች)

ሲን 49

ውስጥ ዴቭ ቤት ጠዋት

(ዴቭና ሜላት ተቃቅፈው ተኝተው የሊንዳና ያሚ ጭቅጭቅ ይሰማል)

ዴቭ

(ቀስ ብሎ ይነቃና ሜላትን ዕቅፉ ውስጥ ሲያገኛት ይደነግጣል)

ወይኔ ጉዴ በቃ ተበላው! አንቺ ሜላት ሜላት ተነሽ! . . . (ብርድ ልብሱን ገልጦ እየነተተ ወደ በሩ ይወስዳታል)

ውጪ ግቢ ውስጥ

(ሊንዳና ያሚ በር በራቸው ላይ ቆመው እየተሰዳደቡ መሲ መፅሀፍ እንደያዘች አስር የግጭት አፈታት መንገዶችን እየጮኸች ታነባለች)

አስር የግጭት መፍቻ መንገዶች

አንደኛ የግጭቱን ምንጭ ማድረቅ

ሁለተኛ ልዩነትን እንደ ውበት መቁጠር

ሶስተኛ...

ሊንዳ

እንግዲህ ምን ታደርጊው የለሽ እንደኔ

ያሚ

ኧረ ለጠላቴም አልመኘው

ሊንዳ

ዝም በይ ነዐል ጡዝ ጡዝ ታዲያ ምን አንጨረጨረሽ ባንቺ ቤት ከቤት ልታስወጪኝ ኣታውቂኝማ ሊንዳ እኮ ነኝ እንኳን የሰውን የዲያቢሎስን ሀሳብ ሳስቀይር አላየሽም

ያሚ

አንቺ ራስሽ ዲያቢሎስ ነሽ

መሲ

ያሚ በቃ አንቺ ግቢ ተያት (ያሚን ቤት አስገብታ ትዘጋባታለች ከዛ ሊንዳንም አስገብታ ትዘጋባታለች ፀቡ በረድ ይላል መሲም ወደ ቤቷ ትገባለች)

ውስጥ ዴቭ ቤት

ዴቭ

(ሶስቱም መግባታቸውን አንገቱን ወጣ አድርጎ ያይና)

በይ ነይ ውጪ አሁን

ሜላት

እሺ ልብሴስ

ዴቭ

ማታ ውጪ አስጥቼዋለው ባከሽ

ሜላት

እና አምጣልኛ እንዲህ ሆኜ ልሄድ ነው ታዲያ

ዴቭ

አቦ ዝም ብለሽ ውጪ በዚ ጭንቅ ሰዓት እንዲህ ሆኜ እንዲያ ሆኜ ትላለች እንዴ

(ይገፈትራታል)

ውጪ ግቢ ውስጥ

(ሜላት ተደብቃ እየወጣች ሁለቱም ከየቤታቸው ወጥተው ፀቡን ድጋሚ ሲጀምሩት እኩል ይገጣጠማሉ)

ሜላት

(ሹልክ ብላ ትወጣለች)

ሊንዳ

እሰይ ሀቢቢዬ እንዲህ ነው እንጂ ይኸው አስደፈርሽን ልጅ እንዲህ ተቸግሮ ሌላ ሴት እስኪያመጣ ድረስ ግቢው ውስጥ ሴት የሌለ ይመስል

ያሚ

(እሳት ጎርሳ ወደ ዴቭ ቤት ትሄዳለች)

ውስጥ ዴቭ ቤት

ዴቭ

(ቤቱን ከውስጥ ቆልፎ ጆሮውን ደፍኖ ይቀመጣል)

ወይኔ ቅሌት! ወይኔ ቅሌት!

ውጪ ግቢ ውስጥ

ያሚ

ከፈተው አንተ ከሀዲ እኔ ላንተ ብዬ ስንት ነገር ልተው አስባለው እኔ ያሚ ላይ ሌላ ሴት

ዴቭ

ኧረ የአክስቴ ልጅ ናት

ያሚ

ዝም በል ! እስኪ አስታውስ ምን አባህ ብለኸኝ ነበር ጭራሽ ማታ እኔን አታለህ ሄደህ ሌላ ሴት ስትስም ነው ያደርከው አንተ እኔን አታለልከኝ ዳዊት ሙት ጀግና ነህ! ቺት ማድረግ እንዴት እንደሆነ አሳይሀለው እሺ !

ሊንዳ

(ያሚ ስታለቅስ ስታይ ታዝንላት ትጀምራለች)

መሲ

(በሯ ላይ ቆማ ራሷን በትዝብት ትነቀንቃለች)

አይ ዳዊት እንደው ምን ይሻልሀል

ሊንዳ

ወይኔ ጉዴ ልጅቷ እያበደች ነው እንዴ (አይዞሽ ልትላት ትሄዳለች) በቃ ያሚዬ ያጋጥማል

ያሚ

(ዞራ ታንባርቅባታለች)

ሊንዳ

(እየጮኸች ወደ ቤቷ ትሮጣለች)

መሲ

(እሷም ደንግጣ ቤቷን ትዘጋዋለች)

ሲን 50

ውስጥ ተካበ ቤት

ሀና

(ለተካበ ከረቫት እያሰረችለት ይታያል)

ተኪ ዛሬ አብሬህ ልዋል

ተካበ

በደስታ ነዋ ሁሉንም ቢዝነሶቼን እያዟዟርኩ አሳይሽና አንድ ጥሩ ቦታ እወስድሻለው

ሀና

(ደስ ይላታል)

በጣም አመሰግናለው (ትስመዋለች) አንዴ ጠብቀኝ ልብስ ልቀይር

ሲን 51

ውጪ ያሚ ቤት በር ላይ ቀን

(ሊንዳ መሲና ዴቭ ያሚ ቤት በር ላይ ቆመው ፈራ ተባ እያሉ አንተ ግባ አንቺ ግቢ እያሉ ሲገባበዙ ይታያል በስተመጨረሻ ዴቭ ይገባል)

ውስጥ ያሚ ቤት

ያሚ

(ራሷ ላይ ጨርቅ አስራ ሶፋ ላይ ተኝታ ይታያል)

ዴቭ

(ሲፈራ ሲተባ አጠገቧ ደርሶ ቀስ ብሎ ከተኛችበት ይቀሰቅሳታል)

ያሚ

(ዞር ብላ ታየውና ተነስታ ጥላው መሄድ ትጀምራለች)

ዴቭ

ቆይ ላስረዳሽ

ያሚ

(ትመለስና አፍንጫቸው እስኪነካካ ድረስ ፊት ለፊቱ ትቆምና)

እሺ አስረዳኝ

ዴቭ

(ያልተዘጋጀበት ነገር በመሆኑ ግራ ይገባዋል) እኔ ምን አስረዳሻለው

ያሚ

ውጣ ከዚ ቤት!

ዴቭ

እ

ያሚ

ውጣ!

ዴቭ

(አንገቱን ደፍቶ ይወጣል)

ውጪ ግቢ ውስጥ

(ሊንዳና መሲ በር ስር ተለጥፈው እያዩ ዴቭ ይወጣል)

ሊንዳ

እ.. ምን አለች

ዴቭ

አልፏቸው በንዴት ወደ ቤቱ ይሄዳል

(እነሱም ተከትለውት ይሄዳሉ)

ሲን 52

ውጪ መንገድ ላይ ቀን

(ተካበ የያሚን የተዘጋ ኮስሞቲክስ ቤት ጨምሮ የተለያዩ ቦታ ያሉትን ቢዝነሶች ለሀና ሲያሳያት ይታያል)

ሲን 53

ውስጥ ዴቭ ቤት ቀን

(ሊንዳ መሲና ዴቭ ቁጭ ብለው ይታያል)

ዴቭ

በቃ የሆነ ነገር አድርጉ እንደምወዳት ታውቃላቹ አይደል

ሊንዳ

በነገርህ ላይ ያሚ ሀገር ይያዝልኝ ስትል ዝም አልኩኝ እንጂ ሀቢቢ ሙት ! እኔ ራሱ በጣም ነው ያዘንኩብህ

ዴቭ

አንቺ ደግሞ ምን ሆንኩኝ ልትዪ ነው

ሊንዳ

ማለቴ እኛ ስጡኝ ብለህ የከለከልንህ ነገር የለ ሴት ይዞ መምጣቱ ለምን እንዳስፈለገ አልገባኝም እኔ ሊንዳ እንኳን ላንተ ለግቢዬ ልጅ ይቅርና ለሙሉ የሀገሬ ወንዶች እምቢ እላለው አልልም !

ዴቭ

ያንቺ እሳትነት ደግሞ በጣም በዛ ፈጣሪ ያብርድልሽ !

መሲ

ስሙ! ምነው እንደዚ ጓደኝነት ቀለለባቹ ምነው እህትነት ወንድምነት የሚባለው ነገር እናንተ ጋር ቦታ አጣሳ ዝም ብሎ ካገኙት ጋር

ሊንዳ

ስነ ስርዓት ሴትዮ እንዳላጥረገርግሽ ሆ! እኔንም ጨመረችኝ እኮ ዴቭዬ

መሲ

እኔና አንቺ በኋላ እናወራለን ዴቭ ያሚ ከህደት ያለችው ነገር ያንተ ባህሪህ ነው:: ይቅርታ ብታደርግልህ እንኳን ነገ ተመልሳቹ መጣላታቹ አይቀርም ስለዚህ በመጀመሪያ ባህሪህን ቀይር

ዴቭ

አሁን ታስታርቁኛላቹ አታስታርቁኝም

ሊንዳ

እኔ አንድ ሀሳብ አለኝ . . ከዚ ሁሉ ለምን አንጠጣም

ሲን 54

ውስጥ ሊንዳ ምሽት በቤት ምሽት

ዴቭ

(ጨብ ብሎ እየጠጣ ይታያል)

ኧረ እዚ ቤት ጨምሩልን እንጂ ምንድነው እሱ አሀ!አሀ! ሊንዳ ነይ ወደዚ

ሊንዳ

ወይኔ ጉዴ ጠራኝ እኮ ሊጠይቀኝ ይሆን

መሲ

ኧረ መጠጥ ጨምሩልኝ ነው ያለው ሆ! እንዳንቺ ደግሞ እህል ውሀ የሆነበት ሰው አይቼ አላውቅም

ሊንዳ

እህል ውሀም ባይሆን እህል የሚበላው ለዚው አይደል ቆይ አስተናግጂው መጣው

(ጠርሙስ ይዛ ትሄዳለች)

ዴቭ

ገና ለገና ጎረቤት ነንና አይከፍልም ብለሽ ነው እንዲህ ባዶ ብርጭቆ አሳቅፈሽ የምታስቀምጪኝ በገንዘቤ ነው የምጠጣው እሺ ማንም ስፖንሰር እንዲያደርገኝ አልፈልግም ይኸው ገንዘብ

(ከኪሱ በርከት ያሉ የብር ኖቶች አውጥቶ ባልኮኒው ላይ ይዘረግፈዋል)

ሊንዳ

ሀቢቢ ሙት እንዳንቀያየም ይሄን ብር ወደ ኪስህ መልስ እኔ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ገንዘቤ

ዴቭ

ስነ ስርዓት! ይሄን ሲሉ የሚያምርባቸው የህዝብ ልጅ የሆኑ አርቲስቶች ድንበር የሚጠብቁ ሰላም የሚያስከብሩ የፖሊስ አባላት ትውልድ የሚቀርፁ መምህራን... ሌሎችም ናቸው እንጂ መጠጥ በመቸበቸብ ትውልድን ጭስ አልባ በሆነ መሳሪያ የምትገዱ አንቺ እንዴት ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብሽ የሚሆነው እስኪ በሞቴ ይቺን ብቻ መልሽልኝ

ሊንዳ

ሀቢቢ ደግሞ ኳስ በመሬት አርገው እንጂ

ዴቭ

ነገሩ ተይው አንዳንድ መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አሉ ይልቅ ሙዚቃውን ሞቅ አርጉልንና እየጨፈርን ሀዘናችንን እንርሳበት

(ሙዚቃ ይቀየራል ዴቭ ብቻውን አዝማ ዳንሶች ሲደንስ ቤት ውስጥ ያሉ ጠጪዎች ፈገግ እያሉ ይመለከቱታል)

ሊንዳ

መቼስ እንዲህ ሰክሮ ብቻውን ማደር የለበትም

መሲ

ስነ ስርዓት ሊንዳ ! በኋላ ከኔ ጋር ነው የምትጣይው ነገሩ እኔ እያለው መች አጠገቡ አስደርስሽና . . . ሽንት ቤቱ የቱ ጋር ነው

ሊንዳ

ይኸው በዚ ጋር ነው

መሲ

(ትሄዳለች)

ሊንዳ

(ከደረቷ ውስጥ አንዳች ዱቄት አውጥታ ለስላሳው ውስጥ ትጨምርባታለች)

እንዲህ ካላደረኩ ለሊቴን ነው የምታበላሽብኝ ወይ አትበላ ወይ አታስበላ ሆ! እንደኔ ተቸግረሽ እይው እንዳልልሽ ታሳዝኚኛለሽ

መሲ

(መጥታ ትቀመጣለች)

ሊንዳ

ያዥ እስኪ ለስላሳም ቢሆን ችርስ ልበልሽ እንጂ ምን አደርጋለው

(አጋጭተው ይጠጣሉ)

ውይ ዴቭዬ ብቻውን ሆነ እስኪ ትንሽ ላስደንስው

(ሊንዳ ከዴቭ ጋር ስትደንስ ይታያል)

መሲ

(ራሷን እንደማዞር አፏ እንደመድረቅ ይልባትና ቀስ በቀስ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን የሊንዳን መጠጥ እያነሳች መጠጣት ትጀምራለች)

ሊንዳ

(ዳንስ ጨርሰው ከዴቭ ጋር ይተቃቀፋሉ)

ዴቭ

(ወደ ቦታው ሄዶ ተቀምጦ መጠጣቱን ይቀጥላል)

ሊንዳ

(ወደ መሲ ሄዳ ለዳንስ ትጋብዛታለች) አሁን ደግሞ ካንቺ ጋ እንጨፍር መሲዬ

መሲ

(ራሷን ስታ ሰከራለች) እኔ እምቢየው የባህል ዘፈን ካልሆነ አልደንስም

ሊንዳ

(ወደ ዲጄው ዘወር ብላ የባህል እንዲያረገው ትነግረዋለች አሳ በለው በለው የሚለው የማንአልሞሽ ዲቦ ሙዚቃ ይከፈታል)

መሲ

(ከተቀመጠችበት ተነስታ እንደ ማን አልሞሽ የቤቱን ዙሪያ በሚገርም ፍጥነት ትሽከረከረዋለች ቤት ውስጥ ያሉት ተጪዎች ወንበራቸውን ወደ ጥግ ይሰበስባሉ)

ዴቭ

ማነው ቬንትሌተሩን የለኮሰው አጥፉት እንጂ . . በዚህ ሰዓት ንፋስ ትለቃላቹ ስንት የተለፋበትን ስካር ልታጠፉት ነው እንዴ (ዞር ሲል መሲ እየተሸከረከረች ሊንዳ ይዛ ልታስቆማት ስትፍጨረጨር ያያል) እንዴ የም አባሮሽ ነው የማየው መሲ አንቺ መሲ (ዞራ እስክትመጣ እጆቹን ዘርግቶ ይጠብቃትና ልክ ሲይዛት ሁለቱም ተያይዘው ይወድቃሉ)

መሲ

አንተ ዴቭ ጣልከኝ የሆንክ ሰካራም

ዴቭ

ጭራሽ እኔን ሰካራም ያኛውን ሰውዬ ሆንሽብኝ እኮ

መሲ

የትኛውን

ዴቭ

ያኛው ነዋ ፈሱን ድም አድርጎት ማነው የፈሳው ያለውን

ሊንዳ

(ከት ብላ ትስቃለች)

መሲ

ሂድ ወደዛ እሺ ፈሳም!

(ለሶስት ተያይዘው ሲጨፍሩ ይታያል)

ሲን 55

ውጪ ግቢ ውስጥ እኩለ ሌት

(ግቢው ውስጥ እየዘፈኑ ይገባሉ)

መሲ

በቃ ! በቃ ድምፅ ቀንሱ ያሚን እንዳንረብሻት

ዴቭ

ትረበሻ ! ትረበሽ! ያሚ አንቺ ያሚ . . . (ወደ በሯ አካባቢ ቆሞ እንድትሰማው ያወራል) ስሚኝማ እንደው ትንሽ ጊዜ ብትሰጪኝ ምን ትሆኛለሽ እንደው ትንሽ! ስንት ነገር አውርተን ስንት ዕቅድ አውጥተን ባንዲት ቀን ስህተት እንዲህ ጥንብ ርኩሴን ታወጪኛለሽ እኔስ ማነኝ አትይም እንዴ ነገሩ እኔ እራሱ ማነኝ

(ሊንዳ ወደ ቤቱ ልታስገባው ትታገላለች መሲ ፈንጠር ብላ በሀዘኔታ የሚናገረውን ትሰማለች)

ከሌሎች ነፍ ሴቶች ጋር እኔና አንቺን ሊያጣላ የሚችል ግንኙነት እያለኝ ምኔም ባልሆነች ሴት በሜላት እንጣላ . . . ወይኔ ያሚዬ! ወድጀሻለው እኮ! እራሴን ላንቺ የሚገባ ሰው ለማድረግም እየጣርኩ ነበር ግን (ከዚ በኋላ ያለው ወሬ ምንም የማይያዝ ነው)

(ሁለቱም ተደጋግፈው ወደ ዴቭ ቤት ይገባሉ)

ሲን 56

ውስጥ ዴቭ ቤት እኩለ ለሊት

(መብራት አብርተው ገብተው አልጋው ላይ ዘፍ ሲሉ ይታያል)

መሲ

ዴቭ አንድ ለዕንቅልፍ የሚሆን ቤድ ታይም ስቶሪ ልንገርህና ወደ ቤቱ ልሂድ

ዴቭ

ቀጥይ

መሲ

በአንድ መንደር የሚኖር አንድ ሱፍ ለባሽ ዕብድ ነበር

ዴቭ

አንቺ ደግሞ ምንም የማይመስል ነገር ነው የምታወሪው ዕብድ ደሞ ከመች ወዲህ ነው ሱፍ የሚለብሰው እንኳን ሱፍ ፓንት ራሱ ላይለብስ ይችላል

ሊንዳ

ዝም አትላትም ሀቢብዬ እኔ ብነግርህ ይሻላል

ዴቭ

አይ ይቅርብኝ አንቺ ደግሞ ቬሎ የምትለብስ ዕብዲት ነበረች ልትይኝ ነው

ሊንዳ

ኧረ አይደለም . . አስር የዴቭ ደረት መሀል መርመስመስ ሱስ የሆነባቸው ጣቶች ነበሩ ከዛ እነዛ ጣቶች (ደረቱ ውስጥ ጣቶቿን ታርመሰምሳቸዋለች)

ዴቭ

(በአንዴ የሚገርም እንቅልፍ ውስጥ ይገባል)

መሲ

እኔ የዚህ ድርጊት ተባባሪ አልሆንም! (ተነስታ ወደ ቤቷ ትሄዳለች)

ሊንዳ

(በደስታ ትሰክራለች) ተገኘች ይቺ በከል ሀቢቢ! ዛሬማ ወንብህ እስኪንቋቋ ድረስ መቅኔህን ስመጥልህ ነው የማድረው (ሰውነቱን ጨመቅ ጨመቅ እያረገች) ሀቢቢ ሙት አለቀልህ! (ልብሷን ማወላለቅ ትጀምራለች)

ሲን 57

ውስጥ መሲ ቤት ለሊት

(መሲ ቤት ውስጥ ጫማዋን አውልቃ አልጋ ላይ ትወጣና በስካር መንፈስ መፅሀፍ አነባለው ብላ ስትጃጃል ይተያል)

መሲ

መቼስ መፅሀፍ ሳላነብማ መተኛት የለብኝም (*መፅሀፍ ገልጣ ፊደላቱ ይንሳፈፉባታል*) ፊደሎቹ ወዴት ነው የሚሄዱት (ከድና ታስቀምጠውና ልትተኛ ብላ የሆነ ነገር ውስጧን ይከነክናታል ተነስታ ትወጣና ወደ ያሚ ቤት ሄዳ ታንኳኳለች)

ውጪ ያሚቤት በር ጋር

ያሚ

(በር ትከፍታለች)

መሲ

ያሚዬ ይቅርታ ከፅንቅልፍሽ ስለቀሰቀስኩሽ እጅግ በጣም አስቸኳይ ስለሆነ ነው በአሁኑ ሰዓት ሊንዳ ዴቭ ቤት ውስጥ ትገኛለች ልጋብዛቹ ብላ ቤቷ ወስዳን ዛሬማ ሀቢቢን አጓጉል ካላደረግኩት እኔ ሊንዳ አይደለሁም ስትል ሰምቻታለው ስለዚህ እንድትታደጊው ልነግርሽ ነው የመጣሁት በተረፈ ደህና እደሪ

(እየተንገዳገደች ወደ ቤቷ ትገባለች)

ያሚ

(የመሲ ቤት በር እስኪዘጋ ቆማ ታይና ትንሽ ወደ ዴቭ ቤት ራመድ ትልና የራሱ ጉዳይ ብላ ተመልሳ ወደ ቤቷ ገብታ በሩን ትዘጋዋለች)

ሲን 58

ውስጥ ዴቭ ቤት ለሊት

ሊንዳ

መጣሁልህ ሀቢቢ

(ሻወር ወስዳ ሰውነቷ ላይ ፎጣ አገልድማ እየተንገበገበች ወደ ዴቭ እየሄደች በር ይንኳኳል ትከፍታለች)

ያሚ

(ዝም ብላ ትቆማለች)

ሊንዳ

(የታችኛው ከንፈሯን በስሱ ነክሳ ዓይኖቿን ስልምልም እያረገች በአፍንጫዋ ትተነፍሳለች)

ወይኔ ሀቢቢ እንዴት የልብ አድርስ ልጅ እንደሆነ ልነግርሽ አልችልም! አንጀቴ ቂቤ ጠጣ ነው የምልሽ! አንጀቴን አራሰው!(የበር መዘጋት ድምፅ ይሰማል ሊንዳ ዓይኗን ስትገልጥ ያሚ አጠገቧ የለችም ቤቷ ገብታ በሩን ትዘጋዋለች) የታባሽ ሰራውልሽ (ቤቱን ትቆልፈውና ወደ አልጋው ሄዳ ዴቭን ትቀሰቅሰዋለች) ሀቢቢ ሀቢቢ አንተ ሀቢቢ

ዴቭ

(እየተጨናበሰ ተነስቶ ይቀመጣል)

ሊንዳ

(በሁለት እግሮቹ መሀከል መሬት ላይ ተንበርክካ ሸቅብ ወደ ላይ ታየዋለች)

አሁን አንድ ነገር ላሳይህ ነው አይንህን በደምብ ግለጥ (ያገለደመችውን ፎጣ ለመፍታት እጇን ወደ ደረቷ ትልካለች)

ዴቭ

(የሆነ ስሜት ይተናነቀዋል)

ሊንዳ ...

ሊንዳ

ወዬ ሀቢቢዬ

ዴቭ

(ፊቷ ላይ ያስመልስባታል)

ሊንዳ

(ፊቷ በሙሉ ከዴቭ አፍ በወጣው ወፈር ያለ ፈሳሽ ይሸፈናል)

ሲን 59

ውጪ እናኑ ግቢ ቀን

(ዴቭ በንዴት ራመድ ራመድ እያለ ወደ ግቢው ሲገባ እናኑን ፊት ለፊት ያገኛታል)

ማሚ አየሽ አይደል እቺ ሜላት የምትባል ልጅ የምትሰራኝን ስራ

እናኑ

እስኪ መጀመሪያ ና ሳመኝ

ዴቭ

(አጠገቧ ሄዶ ዝም ብሎ ይቆማል)

እናኑ

(አገላብጣ ከሳመችው በኋላ) ደሞ ምን አደረገችኝ ነው የምትለው

ዴቭ

አንቺ ነሻ ቤቴን ነግረሻት እንዳለ ህይወቴን አመሰቃቀለችው

እናኑ

ምን አድርጋ

ዴቭ

እኔጋ አድራ ስትወጣ ግቢው ውስጥ የምወዳት ልጅ ነበረች አየቻት! ይኸው አሁን አይንህን ለአፈር ብላኛለች

እናኑ

እና ምን ይጠበስ

ዴቭ

እንዴ ምንድን ነው እማሚ ደግሞ(እንደ ህፃን ልጅ ይነፋነፋል)

እናኑ

ደሞ ደህና የተስተካከለ ኑሮ እንዳለው ሰው ህይወቴን አመሰቃቀለችው ይላል እንከፍ! ውጣልኝ አሁን ከዚ

ዴቭ

እኔ በራሴ ምርጫ ሰው መውደድ አልችልም እንዴ

እናኑ

(ሽመል አንስታ ታሯሩጠዋለች)

ሲን 60

ውስጥ ዴቭ ሱቅ ቀን

ጃሚ

(ወደ ሱቁ እሳት ለብሳ ትገባለች) ዳዊት የታለ

ነፂ

ማነው ደግሞ ዳዊት

ጃሚ

(ሽጉጥ ታወጣለች) ማን እንደሆነ አታውቂም

ነፂ

ኧረ አውቃለው እሱ እኮ ማታ ማታ ነው ገንዘብ ለመውሰድ የሚመጣው እንጂ እዚ አይውልም

ጃሚ

ንገሪው! ከኔ የወሰድከውን ብር አንድ በአንድ ቆጥረህ ትመልሳታለህ ያለበለዚያ ግን ገንዘቤን በልተህ አትቀርም ጥይት ይበላሀል ብላሀለች ጂሚ በይው

ነፂ

እሺ! ይቅርታ

ጂሚ

ዘወር ብላ ታያታለች

ነፂ

ሽጉጧን ፈርቼ መልዕክቷን አልሰማውም አንዴ ትደግሚልኛለሽ

ጂሚ

(ደግማላት ትወጣለች)

ሲን 61

ውጪ ግቢ በር አካባቢ ቀን

(ነፂ ትደውላለች ስልኩ ይጠራል)

ዴቭ

ሄሎ ነፂ

ነፂ

ጂሚ የምትባል ሴትዮ መጥታ ነበር

ዴቭ

ጀምበሬ መጥታ ነበር እንት አወቀችው ሱቁን

ነፂ

ሽጉጥ ደቅና አስፈራርታኝ ነው የሄደችው

ዴቭ

ሽጉጥ !እንዴ ምን ልሁን ብላ

ነፂ

ወይ ገንዘቤን ትበላለህ ወይ ጥይት ይበላህል ብላሀለች

ዴቭ

ምን

(የግቢውን በር ከፍቶ ሲገባ ያሚ በሯ ላይ ከአንድ ወንድ ጋር ተቀምጣ ስትሳሳቅ ያያል . . . ስልኩን ኪሱ ውስጥ ከቶ በንዴት በሩን በሀይል ዘግቶ ይወጣና ትንሽ ከተራመደ በኋላ ድንጋይ አንስቶ ይመለሳል፤ ከዛም ሀሳቡን ቀይሮ ድንጋዩን ጥሎ ስልክ እየደወለ ይሄዳል)

ሄሎ ማቲ መኪናህን እፈልጋለሁ.....

ሲን 62

ውጪ መፅሀፍ ተራ ቀን

መሲ

እሺ ምን አይነት መፅሀፍ ልስጥህ

ሳሚ

(ዙሪያ ገባውን ከቃኘ በኋላ)

ፓፒዮ የሚለውን መፅሀፍ አለሽ

መሲ

(ፊት ለፊቷ መፅሀፉ እያለ እንዳላየ ትሆንና)

አንተ ደግሞ ሁሌ የሌለኝን መፅሀፍ ነው የምትጠይቀኝ ቆይ እስኪ የአባቴ ጓደኛ ጋር ካለ ልፈልግልህ

(ትወጣለች)

ሳሚ

(እያየችው የለም ብላ ልትፈልግ እንደወጣች ይገባዋል ሀዘን ውስጥ ይገባል መፅሀፍ ሊደብቅ ያነሳና መልሶ ቦታው ያስቀምጠውና ለመሄድ ይነሳል)

መሲ

(ምንም መፅሀፍ ሳትይዝ ትመለሳለች)

ሳሚዬ የለም አሉኝ

ሳሚ

(አንገቱን ደፍቶ)

እሺ አመሰግናለው

መሲ

ልትሄድ ነው

ሳሚ

አዎ

መሲ

እንካ ይሄን መፅሀፍ ልጋብዝህ አንብበህ ትመልሳለህ

ሳሚ

ይቅርታ ግብዣው ይቆየኝ

(ይሄዳል)

መሲ

(እሷም አዝና ወደ ሚሄድበት መንገድ ትመለከታለች)

ሲን 63

ውስጥ ዴቭ ሱቅ ቀን

ዴቭ

(የሱቁን ዕቃዎች ተለቅ ወዳለ ማዳበሪያ በፍጥነት እየከተተ ይታያል)

አፍጥኝው! አፍጥኝው!

ነፂ

ስንት ደምበኛ ያለው የለመደ ሱቅ ነው ሌላ ቦታ መቀየሩ ለምን አስፈለገ

ዴቭ

አንዳንድ መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አሉ ዝም ብለሽ ቶሎ ቶሎ ከተች አለበለዚያ ጥይት ይበላሻል

ነፂ

(በሚገርም ፍጥነት ዕቃዎቹን መክተት ትጀምራለች)

ሲን 64

ውስጥ ሊንዳ ግሮሰሪ ምሽት

ሊንዳ

(ድብር ብሏት ብቻዋን እየጠጣች ይታያል)

ዘኪ

(መጠጡን ይዞ ወደ ሊንዳ ይመጣል)

እህ እንዴት ነው

ሊንዳ

ሰላም ነው

ዘኪ

ጓደኞቼ እኮ ደረት ትወዳለች ሂድና አናግራት ብለውኝ

ሊንዳ

(ቀና ብላ ታየውና ደረቱን በጣቶቿ እየደባበሰች)

ቆንጆ ደረት ነው ለሌላ ቀን ይቀመጥልኝ ዛሬ ጥሩ አይደለሁም

ዘኪ

እሺ

(እንደ ጅል ይስቃል)

ሲን 65

ውጪ እነ ያሚ ሰፈር ጠዋት

ያሚ

(የሰፈር ወንዶችን የሚቀመጡበት ቦታ ሄዳ እያነጋገረቻቸው ተደዋውለው ሲሰባሰቡ ይታያል)

ሲን 66

ውስጥ ተካበ ቤት ጠዋት

(ተካበ ቀለል ያለ ቱታ ለብሶ ይታያል ሀና ጥንቅቅ ብላ ለብሳለች፡፡ ቁርስ ሰዓት የሀብት ምዝገባ እያደረጉ ይታያል)

ተካበ

ተለቅ ተለቅ አድርጎ እየጎረሰ ብቻውን እየተሸማ ሲበላ ይታያል)

ሀና

(ወረቀት እና እስኪሪብቶ ይዛ ትፅፋለች) እሺ ሌላስ

ተካበ

ሌላው ያሚ የምትባል ልጅ ያለችበት ኮስሞቲክስ ቤትና አን 500 ካሬ መኖሪያ ቤት

ሀና

የሚገኝበት ቦታስ

ተካበ

ስንሄድ እስከነ ቤት ቁጥሩ ትመዘግቢዋለሽ (ከንፈሩን በሶፍት ይጠራርጋል) አሁን አንቺ ውጪ መዋል ከጀመርሽ ሌላ ቅምጥ ሼፍ ማምጣት ሊኖርብኝ ነዋ (የምግብ ሰሀኑን አንስቶ ለሀና ይሰጣታል)

ሀና

(ከተካበ የተረፈውን ምግብ ትበላለች)

ሲን 67

ከዴቭ ቤት ወደ ግቢ ጠዋት

(የሜሪ አርምዴ ማን አባቱ ያዘኛል ምን የጎበረበት

በገዛ ገላዬ እሳት ባነድበት **የሚለው ዘፈን ይደመጣል)**

ዴቭ

(ከፅንቅልፉ ተነስቶ ልብሱን ለባብሶ ሊወጣ በሩን ይከፍታል)

ያሚ ቤት በር ላይ

(ወደ አራት ወንዶች ይታያሉ አንዱ አጠገቧ ቁጭ ብሎ ጉንጯን ይስማታል ሌሎቹ ሶስቶቹ ተሰልፈው ተራቸውን ይጠብቃሉ አንዱ ከንፈሩን በምራቁ ያራርሳል ሁለተኛው ቻፒስቲክ ይቀባል ሶስተኛው ማስቲካ አፉ ውስጥ ከቶ ያኝካል)

(ሊንዳና መሲ በራቸው ላይ ሆነው በትዝብት ይመለከታሉ)

ዴቭ

(በንዴት እየጮዘ ስልኩን አውጥቶ ይደውላል)

ሄሎ ሜላት አሁኑኑ ልብሶችሽን ይዘሽ ነይ! . . አው እኔጋ!

(ከቤት ይወጣና እንዳላየ ይሄዳል ከዛም መለስ ብሎ ወደ ያሚ ይጠጋና ማውራት ይጀምራል)

ቆይ ግን ምንድን ነው ፍላጎትሽ ይቅርታ አልኩሽ አይደል እንዴ እንዲህ አይነት የህፃን ጨዋታ ለምን አስፈለገ . . በኋላ ግን ለዕርቅ የሚከብድ ፀብ ውስጥ እንዳንገባ

ያሚ

አታስፈራራ ባክህ! እንዴት እንዳስጠላኸኝ ባየህ

ጎረምሳ 1

አቦ ተዋታ የኔ ተራ ሊደርስ ሲል መጥቶ ይወግማል እንዴ

ጎረምሳ 2

በቃ ላሽ በል እስከዛሬ አይናችን ስር ስትገለጭጫት እኛ አላስ ሆንብህ አልሆንብህም

ጎረምሳ 3

አቦ ይሄ ሰውዬ ሌላ ነገር ውስጥ እንዳይከተን

ዴቭ

(ተመልሶ ወደ ቤት ይገባና ተለቅ ያለ የበር መቀረርቀሪያ ይዞ ይወጣል)

ጎረምሳ 4

እንዴ በፋራው ከች ማለት

(ሁሉም እግሬ አውጪኝ ብለው ይሮጣሉ)

ዴቭ

(አባሯቸው ይመለሳል)

ያሚ

(ወደ እሷ እንዳይመጣ ፈርታው ወደ ቤቷ ትገባለች ዱላውን አስገብቶ በሩን ይቆልፍና ይሄዳል)

ሲን 68

ውስጥ እናኑ ቤት ቀን

ሜላት

እሺ ምን ይሻላል

እናኑ

መጀመሪያውኑ ሲደውልልሽ እንዲህ ብሎኛል ምን ይሻላል ብለሽ አታማክሪኝም ነበር ነገ ዞር በይልኝ እንደሚልሽ እያወቅሽ ከቤተሰብሽ ተጣልተሽ ትመጫለሽ . . . በይ አሁን ተነሽ ከኔ ጋር ሄደን ይቅርታ ጠይቀሻቸው ተመልሰሽ ትገቢያለሽ

ሜላት

በፍፁም አይሆንም! ዴቭዬ ጋርማ እሄዳለው

እናኑ

አትጨማለቂብኝ እንግዲ አይሆንም ብዬሻለው አይሆንም

ሜላት

እንደውም ሄጃለው እናንዬ እንድታውቂው ብዬ ነው እንጂ ያንቺ እገዛ አያስፈልገኝም

(ተነስታ ሻንጣዋን እየነተተች ትወጣለች)

እናኑ

አይ ፍርጃዬ ! እንግዲህ ምን አደርጋለው እሱ ይከተልሽ . . ወይ ፍቅር!

አወይ ፍቅር ዕውር ደሞ ጀመረ

(እያንጎራጎረች ወደ ቤት ትገባለች)

ሲን 69

ውጪ መፅሀፍ ተራ ቀን

ዓይናማነቱ ባይገባቸው

ባያውቁት እንጂ ባይገባቸው

ፍቅርን ዕውር ነው የሚሉ

ፀባይና ዓመሉን ያልተረዱ ሁሉ

(የመፅሀፍት መደርደሪያው ላይ ጭራ እያነፈሰች ሙዚቃው ይደመጣል)

ሳሚ

(እስከዛሬ የወሰዳቸውን መፅሀፍች ይዞ ይመጣል)

መሲ እነዚህ በተለያየ ጊዜ ካንቺ የሰረቅኳቸው መፅሀፍቶች ናቸው . . እባክሽ ይቅርታ አድርጊልኝ

መሲ

(መፅሀፍቶቹን ትቀበለውና ዓይን ዓይኑን እያየች ፀጉሩን ትደባብሰዋለች)

ሳሚ

(አንገቱን እንዳቀረቀረ ይጠይቃታል)

ታውቂ ነበር

መሲ

(አንባቷን በአዎንታ ትነቀንቅለታለች)

ሲን 70

ውስጥ ምግብ ቤት ቀን

ዴቭ

(ምግብ ቤት ውስጥ የነደሉ ዕቃዎችን አጀንዳ ላይ እየፃፈ ደምበ አስከባሪዎች ይመጣሉ)

ደ.አ

ሰላም ማነው ባለቤቱ

ዴቭ

እኔ ነኝ

ደ.አ

በግል ነው በማኅበር ያገኘኸው

ዴቭ

በግል ሆኖ እንደማኅበር ነገርም አለው ቆይ አንድግዜ ልደውል

ደ.አ

የት ተሻለ ጋር ነው የምትደውለው

ዴቭ

አው የተሼ ሰዎች ናቹ እንዴ (ጉቦ ይሰጣቸዋል)

ደ.አ

ሰውዬ ብርህን ወደዛ አርግልኝ! ተሻለ ያልከው ሌባ ከስራ ኃላፊነቱ ተነስቷል ሱቁም እንዲታሸግ ተወስኗል! አሁን ወደ ውጪ በመሆን ትተባበሩኛላቹ

ሲን 71

ውስጥ ያሚ ሱቅ ቀን

ያሚ

(ለአንድ ደምበኛ እየሸጠች ይታያል)

ተካበ

(ከሀና ጋር ይገባና ያሚ ሸጣ እስክትጨርስ ለሀና ሱቁንና አንደዳንድ ዕቃዎችን ያሳያታል)

ደምበኛ ፣

(ገንዘብ ከፍላ የገዛችውን ዕቃ ይዛ ትወጣለች)

ተካበ

ያሚን ጉንጯን ይስማትና የምታግዝሽ ልጅ ይገፍልሽ መጥቻለው ሀና ትባላለች ዘመዴ ነች

ሀና

(ትጨብጣታለች)

ተካበ

አባቷ ባለውለታዬ ናቸው አደራ በደምብ አድርገሽ አስለምጂልኝ እሺ . . ሀኒኞ አንቺም ቀልጠፍ ነው ታዲያ . . . በሉ መልካም ቀን (ይወጣል)

ያሚ

(ብቻዋን ፈገግ እያለች ነገር መብላት ትጀምራለች)

የሚገርምሽ እኔን አስለምዳኝ የተባረረች ልጅ ነበረች ስንት ጊዜ አልፎ ዛሬ ትዝ አለችኝ

ሀና

አይደል ያው አንዱ ሲመጣ አንዱ ይሄዳል ምን ታደርጊዋለሽ

ሲን 72

ውስጥ ዴቭ ቤት ምሽት

ዴቭ

ቤት አውቀዋል

ሜላት

አው! አብርሽዬ ከዚ በኋላ አባቴ ብለሽ እንዳትመጪ አለኝ

ዴቭ

ታዲያ እንደዛ እያሉሽ እንዴት ትመጫለሽ ከአባትሽ እኔ እበልጥብሻለው

ሜላት

አንዳንድ ጥያቄዎች መልስ የላቸውም . . . ለማንኛውም የወለደ አይጨክንም አያሳስብህ

ዴቭ

እሺ አሁን አንዳንድ የምታግዢኝ ስራዎች አሉ (ሱቆቹን እንድትቆጣጠርለት አጀንዳው ላይ የፃፉቸውን የወጪና ገቢ ዝርዝሮችን ያሳያታል)

ሲን 73

ከግቢ ወደ ያሚ ቤት ምሽት

ሊንዳ

(ከስራ መልስ ወደ ቤት ልትገባ ትልና ሀሳቧን ቀይራ ወደ ያሚ ቤት ሄዳ ታንኳኳለች መልስ ስታጣ በሩ ዝግ መሆኑን ለማረጋገጥ እጀታውን ስታዞረው ይከፈታል)

ያሚ

(የተበላሸውን ብርቱካን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ እየተመለከተች በሀሳብ ጭልጥ ብላ ይታያል)

ሊንዳ

(አንገቷን አስገብታ ያሚ አለመተኛቷን ስታይ ወደ ውስጥ ትገባለች)

መግባት እችላለው

ያሚ

(አይታት ዝም ትላለች)

ሊንዳ

(ገብታ ትቀመጣለች፤ከዛም የተበላሸውን ብርቱካን አንስታ በብርቱካኑ ውስጥ ራሷን ፈልጋ እስክታገኘው ድረስ ትከዝ ብላ ትቆያለች)

0 አንድ ወቅት ይሄ ብርቱካን ጣፋጭና ለዓይን የሚያምር ነበር 1 አሁን ግን የማማሩም ሆነ የጥፍጥናው ጊዜ አልፏል 2 አሁን ደሞ ተራው የሌሎች ብርቱካኖች ነው 3 ሁሉም በጊዜው ሲሆን ያምራል ::

ሊንዳ እየተናገረች ተደራቢና ተለዋዋጭ ሆኖ የሚታይ

0 (ከሌሎች ያልበሰሉ ብርቱካኖች አንድ የበሰለ ብርቱካን ይታያል)

ዴቭ

1 አንቺ ማለት ይሄ ብርቱካን ነሽ

ብርቱካን ትርንጎ መሳይ በስሜት ልቤ አንቺን ሲያይ.... ያዥ (ይወረውርላታል)

ሜላት

2 (ትቀልበውና) ይቺን ብርቱካንማ አስቀምጣለው

ዴቭ

3 እንዲህ እንዳማረ ቢቆይ እንዴት ጥሩ ነበር

ሊንዳ

ያሚ . . ይቅርታ ልጠይቅሽ ነው የመጣውት . . . በርግጥ ከዴቭ ጋር ምንም የተፈጠረ ነገር የለም ከተካበ ጋር ግን...

ያሚ

(በተቀመጠችበት ጥላት ወደ መኝታ ክፍሏ ትሄዳለች)

ሲን 74

ውጪ ቤተ ክርስቲያን ጠዋት

ሜሮን

የሌሊት ዕንቅልፍ ማጣቴን የቀን መባዘኔን አይተህ ከጎኑ ስላረከኝ አምላኬ ሆይ አመሰግንሀለው! ቢያንስ አሁን አብሬው ነኝ

ሲን 75

ውጪ እናኑ በር ጋር

ምርቃት

(ማስቲካዋን እያንቀጫቀጨች)

ሀይ ማዘር ዴቭ አለ እንዴ

እናኑ

(ከጥፍር እስከ ፀጉሯ ከተመለከታት በኋላ)

ቆይ ቢኖርስ ምን ልትሆኚ

ምርቃት

ያው ሰው የሚሆነውን ነዋ

እናኑ

እግዚያ መዓት! ኧረ ተዉ የዘንድሮ ልጆች ተዉ! ምናለ ቀስ ብላቹ ብታድጉ

ምርቃት

እንዴ ማዘር ትንሽ ልጅ መስዬሽ ነው እንዴ ቆይ ላሳይሽ (ስልኳ ላይ ካሉ ፎቶዎች የልጆቿን መርጣ ታሳያታለች) ይቺኛዋ የመጀመሪያ ልጄ ነች አምስት አመቷ ነው አሁን አባቷ ጋር ነው የምትኖረው ይሄኛው ደሞ ሁለተኛ ልጄ ነው ሶስት አመት ሆነው መሰለኝ አባቱ ከዶኝ ለእናቴ ሰጥቻታለው

እናኑ

እና አሁን ሶስተኛሽን ልትወልጂ ነዋ የመጣሽው

ምርቃት

(ስልኳ ይጠራል)

ወዬ ዳኒዬ . . አትለኝም! እንዴ የናንተን ዴይ ፓሪማ እንዴት እቀራለው መጣው! መጣው! ቻው ማሚዬ ዴቭን ሀይ በይልኝ ሌላ ቀን እመጣለው

እናኑ

አቤት! አቤት! ዛሬ ደሞ ምኗን ነው ያመጣብኝ (ንግግሯን ትንሽ ካስመሰለች በኋላ) ቅንጣቢ የሰው ምርቃት!

ሲን 76

ውጪ ግቢ ውስጥ ቀን

ሜላት

(የዴቭን ልብስ ልታጥብ ኪስ ስትፈታትሽ ትታያለች)

ሲን 77

ውስጥ ያሚ ሱቅ ቀን

(ተካበ ወደ ኮስሞቲክስ ሱቁ ይገባል ሁለቱ ጣውንቶች ሀና እና ያሚ በክፉ ዐይን እየተያዩ ተቀምጠዋል)

ተካበ

(ያሚን ሊስማት ያጎነብሳል)

ያሚ

(ጉንጯን ታዞርበታለች)

ተካበ

(በንቀት ገላምጧት ወደ ሀና ይሄዳል)

ሀና

(ከያሚ ተቃራኒ በሆነ ስሜት ተነስታ ትስመዋለች) ተከዬ ውዴ

ተካበ

እሺ እንዴት ነው እየለመድሽ ነው

ሀና

ስራው ያን ያህል የተወሳሰበ አይደለም ስለዚህ ከዛሬ በኋላ አታስፈልገንም

ተካበ

እና ትባረር

ሀና

አው ትባረር

ተካበ

ሂጅ አንቺ! ሂጅ ውጪ!

(እያበሻቀጡ፣እየተሸካኩና እየተሳለቁ ያስወጧታል)

ያሚ

(ከሱቁ ላትመለስ ትወጣለች)

ተካበ

(ወደ ሀና ዞሮ ያስጠነቅቃታል) አንቺም እንደሷ እንዳትባረሪ ፀባይሽን አሳምሪ

ሲን 78

ከግቢ ወደ ዴሽ ቤት ውስጥ ቀን

ሜላት

(ቤቱን ስታስተካክል በተለይም እናኑ በእጇ የሰፋችለትን የዳንቴል አልጋ ልብስ ስታነጥፍ ይታያል)

ሲን 79

ፍላሽ ባክ ውስጥ እናኑ ቤት ቀን

(ቤት ውስጥ ዴቭና ሜላት ተቃቅፈው እየተላፉ ይታያል)

እናኑ

(የአልጋ ልብስ በኪሮሽ ሰርታ ስትጨርስ ይታያል ከዛም ሜላትና ዴቭን ታለብሳቸዋለች)

ይኸው ሰርቼ ጨርስኩ

ሜላት

እናንዬ ለዴቭ ነው እንዴ ስትሰሪ የነበረው

እናኑ

ታዲያስ! ስማ አንተ ከንቱ ይሄን አልጋ ልብስ ከሜላት ውጪ ከሌላ ሴት ጋር ትለብሰውና ወዬውልህ

ዴቭ

ከሜላት ጋር ግን መጋፈፍ ተፈቅዶልኛል ማለት ነው ነይ አንቺ

(አልጋ ልብሱ ይሸፍናቸዋል)

እናኑ

(አፍራ ፊቷን ትይዛለች)

ከፍላሽ ባክ መልስ

ሜላት

(አልጋው ላይ ተቀምጣ በረኸርሙ ትተነፍሳለች)

ሲን 80

ውስጥ ቦሌ ሚካኤል የዴቭ ልብስ መሸጫ ሱቅ ቀን

ዴቭ

(ከትዕዛዙ ብር ይቀበልና)

ይሄ ብቻ ነው ያለው

ትዛዙ

አዎ

ዴቭ

በዚ ሁኔታ የቤት ኪራይ እንኳን መክፈል ከባድ ሊሆንብኝ ይችላል

ትዛዙ

ገበያ ቀዝቅዟል

አንተ ነህ እንጂ የቀዘቀዝከው እስኪ ሌላው ቢቀር ደህና ነገር ልበስ ፀጉርህን ፈርዝ ይሄን ፊት ይዘህ እየመጣህ ድሮስ ላይቀዘቅዝ ነው

(ከሱቅ ብር ተቀብሎ እየወጣ ስልኩ ይጠራል)

ሜላት

ዴቭዬ ምሳ ሰርቼ እየጠበቅኩህ ነው

ዴቭ

ምሳ ቤት በልቼ አላውቅም አልመጣም

ሲን 81

ውጪ መፅሀፍ ተራ ቀን

ሳሚ

(የተሸጠበትን ይሰጣታል) ስላመንሽኝና ይሄን ዕድል ስለሰጠሽኝ አመሰግናለው በቃ ልሂድ (ለምዶበት ፊት ለፊቷ ሻግ ይመታል)

መሲ

(ሳቋ ያፍናታል)

ሲን 82

ውጪ መንገድ ላይ ከሰዓት

ያሚ

(ብቻዋን ስትጓዝ ዴቭ ጨረቃና ፀሀይ ምስክር ይሁኑኝ ያለው በምልሰት ይላታል)

ሲን 83

ውስጥ ዴቭ ቤት ማታ

ዴቭ

(ውጪ መጠጥ ቀማምሶ ትንሽ ሞቅ ብሎት ይገባል)

ሜላት

(ሶፋ ላይ ቁጭ ባለችበት ዕንቅልፍ ይዟት ሄዶ በር ሲከፈት ትነቃለች)

መጣህልኝ ዴቭዬ

ዴቭ

ስለመሸ ልተኛ መጣሁ እንጂ ላንቺ ስል አይደለሁም መጣህልኝ በላህልኝ ጠጣህልኝ ምንድን ነው ስሚ አንቺ ለኔ እኔ ላንቺ ስንል ምንም የምናደርገው ነገር የለም ሁሉም ለራሱ ሲል ነው የሚኖረው አይደለም

ሜላት

እሺ

ዴቭ

ቆይ ቆይ እንተማመን አንቺ የምትለብሺው የምትበይው የምትጠጪው በአጠቃላይ የምትኖሪው ለኔ ስትይ ነው

ሜላት

አው

ዴቭ

እቺ ልጅ ደህና ነሽ ግን ወይስ ሳላውቀው ያስነካሁሽ ነገር ይኖር ይሆን አሁንስ ራሴን እጠራጠረው ጀመር

ሜላት

ደሞ ቆንጆ እራት ሰርቼልሀለው

ዴቭ

ቲሽ! አጉል እናት እናት አይሰራራሽ ባክሽ

(ትቷት ይተኛል)

ሜላት

አጉል! እኔ ለማስመሰል ብዬ አላደረግኩት ለምን እንዲህ ይለኛል

ዴቭ

ደሞ ይሄን ማን አንጥፊ አለሽ ይሄስ ደሞ ምንድን ነው (አጣጥፋ ያስቀመጠቻቸውን ልብሶች ያዘበራርቀዋል) ደሞ እዚ ቁጭ ብለሽ አትቁለጭለጪብኝ ሂጅ ግቢና ተኚ

ሜላት

ለቁርስ የሚሆን ነገር ሳልሰራልህ

ዴቭ

ኡኡይ... (ይጮሀል)

ሜላት

እሺ በቃ አትጩህ ራስህን ያምህል ይኸው እተኛለው በቃ (ትተኛለች)

ዴቭ

(እንደተለመደው ጀርባውን ሰጥቷት ይተኛል)

ሜላት

(አቅፋው ታተኛለች)

ሲን 84

ውስጥ ዴቭ ቤት ጠዋት

(ጀርባውን ሰጥቷት የተኛው ዴቭ ሌሊት ላይ ታሪኩ ተገለባብጦ ሲነጋ ግጥም አድርጎ አቅፏት እየታየ ከውጪ የጭቅጭቅ ድምፅ ይሰማል)

ዴቭ

(ከዕንቅልፉ ይነቃና ሜላትን ዕቅፉ ውስጥ ይመለከታትና ፈገግ ይላል)

ሲን 85

ውስጥ ያሚ ግቢ ጠዋት

(ተካበና ሀና በአንድ በኩል ሊንዳና ያሚ በሌላ በኩል ሆነው እየተጨቃጨቁ መሲ መሀል ላይ ሆና ትገላግላለች)

ያሚ

እንደ ሸንኮራማ መጥጠህ ልትጥለኝ አትችልም

ሊንዳ

አንተ ቅሌታም ሽማግሌ

ሀና

ስነ ስርዓትሽን ያዢ

ሊንዳ

(በአረብኛ ትሰድባታለች) ዝም በይ አንቺ ደግሞ ምን የላት ምን የላት የሆነች ልሙጥ

ተካበ

ምን አለች

ሀና

እኔንጃላት እስቲ ወንድ ከሆንሽ በአማርኛ

ሊንዳ

አግኝቼ ነው ያውም በሀገሬ ቋንቋ አንቺ (ድጋሚ በአረብኛ ታፀዳዋለች)

መሲ

አማርኛ ብለሽ ነበር

ተካበ

አሁን ምንም ንትርክ አያስፈልግም ጨርቄን ማቄን ሳትይ በዚች ሳምንት ውስጥ ቤቱን እንድትለቂ

ዴቭ

(ከቤት ይወጣል)

ምንድን ነው አቧራ የምታስነሱት

ሊንዳ

ሀቢቢዬ ይሄ ሽማግሌ የያሚን ቤት ለሌላ ሴት ሊሰጠው ነው ያሚን እንደ ዕቃ አውጥቶ ሊጥላት ነው

ተካበ

አሀ ለካ ይሄ ልክስክስም አለ እንደውም ጥሩ ነው የነዳናው ብርድ እሱ ዕቅፍ ውስጥ ሲሆን ትንሽ ቀነስ ይልልሻል

ዴቭ

ምን (በአስፈሪ ሁኔታ ወደ ተካበ ይሄዳል)

ተካበ

(ሽጉጥ ያወጣል)

ሜላት

(ከቤት ስትወጣ ዴቭ ሽጉጥ ተደግኖበት ታያለች ወዲያው ጉልበቷ ይከዳትና ሸርተት ብላ ትወድቃለች)

ሲን 86

ውጪ እናኑ ግቢ ጠዋት

(እናኑ እና አዲሱ ተከራይ ዞላ የዳዊት የቀድሞ ቤቱ በር ላይ ቆመው ይታያል)

ዞላ

ቆንጆ ቤት ነው ወድጀዋለው ታዲያ ቀብድ ስንት ልክፈል

እናኑ

ችግር የለም ስትመጣም ይደርሳል

ዞላ

አይ ቀብድማ ደምብ ነው እኔም እንዳልቀር እርሶም ለሌላ እንዳያከራዩት

(ስምንት መቶ ብር ቆጥሮ ይሰጣታል)

እናኑ

(ብሩን ይዛ ትቆዝማለች)

ዞላ

ምነው ማዘር ቅር ያሎት ነገር አለ እንዴ

እናኑ

የልጇ ቤት ነበር አንድ ቀን ይመለሳል ብዬ ከወጣ ጀምሮ ቤቱን ክፍት አድርጌ ጠበቅኩት ግን አልሆነም እህህ.....

ሲን 87

ውስጥ ዴቭ ቤት እኩለ ቀን

(ሜላት ግንባሯ ላይ ጨርቅ አስራ የዴቭ ጉልበት ላይ ተኝታ ይታያል)

ሲን 88

ውስጥ ያሚ ቤት

(ያሚ ሻንጣዋ ውስጥ ልብስ እየከተተች መሲና ሊንዳ በሀዘን ቆመው ይመለከቷታል)

ያሚ

(በውስጧ የሚመላለስስ አንድ ሀሳብ ድንገት የምታጥፈውን ልብስ እንድትጠየፈው ያደርጋታል ስሜቱ ወደ ለበሰችው ልብስም እየተዘዋወረ ገላዋ ላይ ያለው ልብሷ ሸከም ይሆንባታል)

የማትፈልጉት አሮጌ ልብስ አላቹ

(መሲና ሊንዳ ያለቅሳለሉ)

ሊንዳ

(ዕንባዋን መቆጣጠር አልችል ብላ ትወጣለች)

መሲ

(እሷም ተከትላት ትወጣለች)

ውጪ ግቢ ውስጥ

መሲ

ቆይ ሊንዳ! ሌላው ሁሉ ቢቀር ቢያንስ ከዴቭ ጋር ማስታረቅ አለብን

ሊንዳ

እንዴት አድርገን

ሲን 89

ውስጥ ሊንዳ ምሽት ቤት ምሽት

(ዴቭ መሲ እና ሌሎች ከስተመሮች ሊንዳ ምሽት ቤት ውስጥ ይታያሉ)

ዴቭ

እና በቃ እየተለያየን ነው ማለት ነው

መሲ

ቢሆንም ግን ህይወት ይቀጥላል

ዴቭ

ሰው መለየት እንደዛሬው ከብዶኝ አያውቅም

መሲ

ደስ ይላል! ሰው መሆን ጀመርክ

ዴቭ

ያሚ አትመጣም እንዴ

(ያሚ እና ሊንዳ ይገባሉ)

ያሚ

(የደስታ ብርሀን የሚረጨው ፊቷ የተስፋ መቁረጥ ደመና ከልሎታል ከዚ ቀደም የምትታወቅበት ሽቅርቅር አለባበሷ የለም፡፡ ምሽት ቤት ውስጥ የህብስት ጥሩነህ ዘፈን ይደመጣል)

ዘመናዊው ልብሴ አለፈ ወራቱ

አስጠላኝ ያላንተ ደምቆ መታየቱ

ዴቭ

(ያሚን ሲያይ እሱ ራሱ ሳያውቀው ከተቀመጠበት ይነሳል)

ሊንዳ

(ያሚን ወደ ዴቭ ትወስዳትና ከመሲ ጋር ትቆማለች)

ዴቭ

(ያሚን ፊት ለፊት እያየ አንደበቱ ለቃል ተከልክሎ ባይኑ ብዙ ያወራታል አስፈሪ ፀጥታ ይሆናል)

ሊንዳ

አንቺ መሲ ሰዎቹ እኮ ደርቀው ቀሩ

ዴቭ

(ያሚን ግንባሯን ይስማትና ዕቅፉ ውስጥ አስገብቶ ያወራታል) በርቺልኝ ያሚዬ ከትናንት አይብስምና ነገን እንዳትፈሪ (ከዕቅፉ ያወጣትና ለትዝታ ትቷት ይሄዳል)

ያሚ

(ቁጭ ብላ ታለቅሳለች)

ሄኖክ (ከዕድምተኞች አንዱ)

(ትንሽ መጠጥ ሞቅ ብሎት በሚተሳሰር ንግግር) ሊንዳ እስኪ በዛ ከወይን የሚጣፍጥ ድምፅሽ አንድ ለስለስ ያለ ወለላ የሆነ ሙዚቃ ተጫወቺልን

ሊንዳ

(ቁጭ ብላ የፊልሙ ማጀቢያ የሆነውን ሙዚቃ መዝፈን ትጀምራለች)

ሲን 90

ውጪ መንገድ ላይ ምሽት

ዴቭ

(በጨለማ ውስጥ ብቻውን ሲሄድ ይታያል የሊንዳ ድምፅ የዴቭ ምስል ላይ ተደርቦ ይደመጣል ማጀቢያ ሙዚቃው ፈድ አውት እያደረገ የዳዊት ድምፅ ቮይስ ኦቨር ይገባል)

ሌላ ክንፏን የሰበርኳት ርግብ አለች ቀሪ ዘመኔን ከሷ ጋር ለመብረር እሻለው ስለምትገባኝ ሳይሆን ራስ ወዳድ ስለሆንኩ፡፡ ፈጣሪዬ ሆይ ንፁህ ልቧን ለማልመለስበት ትላንት ሽልማቴ አድርገህ ትሰጠኝ ዘንድ እለምንሀለው ሜላትዬ እወድሻለው!

(የንግግሩ ማብቂያና የቤቱን በር የሚከፍትበት ጊዜ እኩል ይሆናል ቤት ውስጥ ሜላት የለችም ስሟን ጠርቶ ግቢ ውስጥ ቢዘዋወርም አቤት የሚለው ያጣል በስተመጨረሻ ስልክ አንስቶ እና ጋር ይደውላል)

ማሚ ሜላት አንቺ ጋር መጥታለች አሚት ተኝታ ነበር እኮ (ስልኩ ከእጁ ይወድቃል ፅንባ ይተናነቀዋል ካሜራው 360 ይዞረዋል ሜላትን ሲያበሻቅጣት ሲቆጣት ሲገፈትራት ሲያስለቅሳት የነበሩ ትዕይንቶች ከካሜራው ዙረት ፍጥነት ጋር እየተደራረቡ በምልሰት ይታያሉ)

ሲን 91

ውጪ መንገድ ላይ ምሽት

ዴቭ

(የሜላትን ስም እየጠራ መንገዱን ያካልለዋል አንድ ጨለም ያለ ቅያስ እንደታጠፈ ከኋላ ሲከታተሉት የነበሩ ማጅራት መቺዎች ይይዙታል)

ማጅራት መቺዎች

(አንዱ ከኋላ ጥፍንግ አድርጎ ሲይዘው አንደኛው ከፊት ከኪሱ የያዘውን ያለውን ገንዘብ ይዘርፈዋል)

ዴቭ

(ማጅራት መቺዎቹን ለመታገል አይሞክርም ብቻ እየደጋገመ የሜላትን ስም ይጠራል)

ማጅራት መቺዎቹ

(ብሩን ይመልሱለትና አብረውት መሬት ላይ ይቀመጣሉ አሳዝኗቸው፤ለምን አያዝኑ እነሱስ ሰው አይደሉምን)

ሲን 92

ውስጥ ተካበ ቤት ምሽት

(ቤቱ ጨለም ያለና የሚጨንቅ ድባብ አለው ጠረጴዛው ላይ ሶስተኛ አመት በአል የሚል ፅሁፍ ያለበት ኬክ ወይን የተቀዳባቸው ብርጭቆዎች የሚበራ ሻማ እንዲሁም ሀና በእራት ልብስ ይታያሉ)

ሀና

(እጇ ላይ የያዘችውን ትንሽዬ የተጠቀለለ ወረቀት በጥልቀት ትመለከተዋለች)

ሲን 93

ውጪ መንገድ ላይ ማለዳ

ሀና

ከዕድሜዬ ሶስት አመታትን የሰዋሁበት ህይወት ነው ምንም አይነት ችግር እንዲገጥመኝ አልፈልግም

ኒቆ

በዚህ እንኳን ስጋት አይግባሽ ብቻ በኋላ መሸማጠጥ ሲመጣ ነው ችግሩ የዛኔ በህይወት የሚኖረው አንድ ሰው ብቻ ይሆናል እኔ ወይ አንቺ

ሀና

እሺ ቀጣይስ ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ

ዴቭ

ትንሽ ጠብቀን የፍርድ ቤቱን ጉዳይ እንሄድበታለን እኔ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች አዘጋጅልሻለው

ሀና

(ቃል ሳታወጣ ትንፋሷን ውጣ ትዝታለች)

ወደ ቀደመው ሲን

የበር መንኳኳት ድምፅ ይሰማል

ሀና

(ከሀሳቧ ተመልሳ በጥድፊያ ብርጭቆ ውስጥ ዱቄቱን ትከትና ወረቀቱን ወደ ደረቷ ደብቃ ወይኑን ትነቀንቀዋለች ከዛም ራሷን አረጋግታ ትንሽ ፈገግ ትልና በሩን ትከፍተዋለች)

ተካበ

(እየሳማት) አዪ መብራት የለም

ሀና

ኧረ አለ

ተካበ

ታዲያ ምን ጨለማ ውስጥ ያስቀምጥሻል

(ማብሪያ ማጥፊያውን ደጋግሞ ወደ ላይ ታች ሲጫነው መብራቱ አይበራም)

ሀና

እንደውም ጥሩ አጋጣሚ

ተካበ

ደሞ ምን ጉድ ነው እንዲህ ያማረብሽ

ሀና

(ተካበን ያዘጋጀችለት ወንበር ላይ ታስቀምጠውና ወይኑን እየሰጠችው)

እንኳን ለሶስተኛ አመታችን በሰላም አደረሰህ ቸርስ

ተካበ

ሶስት አመት! ሚስት ልትሆኚ ምን ቀረሽ

ሀና

(ትንሽ ፈገግ ትልና) ቸርስ

ተካበ

አይ ወይኑ እንኳን ይቅርብኝ ከውስኪ ወደ ታችማ ጥሩ አይመጣም

ሀና

(ብርጭቆዋን ይዛ መጥታ እየነካካችው) ጠጣ እንጂ ተከዬ

ተካበ

(እንደተለመደው ስሜቱ እያየለበት) አንቺ ደግሞ በቃ ሰው አትሰሚም አይደል

ሀና

(ወይኑን አንስታ ታቀብለዋለች)

ተካበ

(ጭልጥ አድርጎ ይጠጣውና) ነይ በይ አሁን (እየዘፈነና ዋልዝ እያስደነሰ ወደ መኝታ ክፍል ይወስዳታል)

ሲን 94

ውስጥ ተካበ ቤት መኝታ ክፍል ማለዳ

ሀና

(ጭልጥ ብሎ የተኛውን ተካበን እያየች አንዳች ነገር ትጠባበቃለች)

ተካበ

(አስፈሪ የማጓራት አይነት ማንኮራፋት ያሰማል)

ሀና

(ፈራ ተባ እያለች ትቀሰቅሰዋለች)

ተካበ አንተ ተካበ ... አንተ ተካበ!

ተካበ

(በአንዴ አይኑን ቦግ አድርጎ በፊት ከነበረው አቅም ጨምሮ ብድግ ይልና ብርድ ልብሱን አሽቀንጥሮ ይጥለዋል)

ሀና

(በድንጋጤ ተሸማቃ እፍኝ ታክላለች)

ተካበ

(በውስጥ ሱሪው ብቻ ሆኖ እየዘለለና እየጮኸ ከቤት ፣ከግቢና ከመንደሩ ይወጣል፡፡ ያውቁት የነበሩ ሰዎች አንዳንዶች ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሌሎች እሰይ የእጁን አገኘ እያሉት መንገደኞች ደግሞ እየሸሹት ጨርቁን ጥሎ ጎዳናውን እያቋረጠ ሲሄድ ይታያል)

ሲን 95

ከውጪ ወደ ውስጥ መሲ ቤት ጠዋት

መሲ

(የሊንዳን ቤት በር ታንኳኳለች)

ሊንዳ

(በር ስትከፍት መሲን ትመለከታታለች) ወዬ መሲ ምነው ምን ተፈጠረ

መሲ

ዴቭ ቤት ለቋል

ሊንዳ

መች እቃውን ይዞ ምናምን

መሲ

አው ቤቱ ባዶ ነው

ያሚ

(በጣሳ ውሀ ይዛ ከመሲ ቤት ስትወጣ በመጀመሪያ ሊንዳና መሲን ቀጥሎም ክፍቱን ያለውን የዴቭን ቤት ታየዋለች ጣሳውን አስቀምጣ የዴቭን በር ከፍታ ስትገባ በቤቱ ውስጥ አንድም ዕቃ የለም)

ምን አለ ቻው እንኳን ቢለኝ (ታለቅሳለች)

ሲን 96

ውጪ እናኑ ግቢ በር ላይ ጠዋት

ዴቭ

(በር ሊያንኳኳ እጁን ያነሳና በረጅሙ ተንፍሶ ይተወዋል ከዛም የግቢውን በር ተደግፎ መሬት ላይ ዝርግት ብሎ ይቀመጣል)

እናኑ

(ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ነጠላ ለብሳ የግቢውን በር ከፍታ ስትወጣ ዴቭን ታየዋለች)

በስመአብ ወወልድ የፈጣሪ ያለህ ምነው ልጄ

ዴቭ

(እያለቀሰ)ሜላት የት ሄዳ ነው

እናኑ

ልነግርህ ስደውል እኮ ስልክህ አይሰራም ማታ ካንተ በኋላ ደውላልኝ ነበር አታስብ ቤተሰቦቿ ጋር ነው ያለችው

ዴቭ

ምን አለችሽ

እናኑ

አዝናብሀለች እኔንጃ ከዚ ወዲህስ እንደ ድሮው የምትሆንም አይመስለኝም በዚ ላይ አባቷ ሀገር ይያዝልኝ ነው ያለው

ዴቭ

ማሚዬ አንዴ ብቻ አገናኚኝ እንደምንም ብለሽ አንዴ ብቻ

እናኑ

እሺ ከቆሻሻው ላይ ተነስ! ተነስ የኔ አባት አንተ እንኳንም ልቦናህን መለሰልህ እንጂ እኔም ቢሆን እግሯ ላይ ወድቄ እለምልሀለው በል አሁን ሂድና ደህና ልብስ ልበስ ፀጉርህን ፂምህን አስተካክል አበባም ነገር ያዝ አድርግ ታውቂበት የለ እንዴ አንቺ ጮሌ ይሄ ደሞ ምን ይነርሻል በል ተነስ!

ሲን 97

ውጪ አንድ ግቢ በር ላይ ረፋድ

(ያሚ ሊንዳና መሲ ቤት ፍለጋ እየኳተኑ አንድ ተለቅ ያለ ግቢ በር ጋር ይደርሳሉ)

ሊንዳ

(ታንኳኳለች)

ዮናታን

(ረዘም ያለ ፂማም ልጅ በሩን ይከፍታል)

ሊንዳ

የሀቢብቲ እንዴት ነው የሚያምረው

መሲ

የሚከራይ ቤት ይኖራቿል

ዮናታን

አይ የለንም (ወደ ሊንዳ እያየ) ላንቺ የሚሆን ግን አይጠፋም

መሲ

ነይ እንሂድ (ጎትታ ትወስዳታለች)

ሊንዳ

(በአረብኛ ውበቱን ታደንቃለች)

ሲን 98

ውስጥ መጠጥ ቤት ምሽት

(ለወትሮው ወንድ ላይ ሰፍ ትል የነበረው ሊንዳ ሁሉ ነገረ አስጠልቷ ወደ እሷ የመጣውን ወንድ ስትገፋ ይታያል)

ሲን 99

ውጪ እናኑ ግቢ ውስጥ ከሰዓት

እናኑ

(የሀገር ባህል ልብስ ለብሳ ደጅ ላይ ተቀምጣ ይታያል)

ዴቭ

(እስካሁን ፊልሙ ላይ ከነበረው ገፅታ ይበልጥ አምሮበት ሱፍ ለብሶ እቅፍ አበባ ይዞ ወደ ግቢው ይገባል)

እናኑ

እሰይ! እሰይ! እንዲህ ነው እንጂ ልጅ አይ ማማር ናእስኪ ልሳምህ (ግንባሩን ትስመዋለች)

ዴቭ

በቃ እንሂድና...

እናኑ

እስቲ እግዜር ይርዳን... ማነሽ እስኪ ነጠላዬን ወዲህ በይ

ሜላት

(ከቤት ትወጣለች)

ዴቭ

(ደንግጦ ይንበረከካል) ሜ.ሜ.ሜላት

ሜላት

የኔ ጌታ ጉልበትህን ይቆረቁርሀል ተነስ

እናኑ

እኔ እንደው እቺ ልጅ ምን እንደሚሻለኝ እናት እኮ ነች እናት

ዴቭ

(ከአዕምሮው በላይ ይሆንበትና አንገቱን እንደደፋ ይቀራል)

ሜላት

ተነስ ዴቭዬ (ከተንበረከከበት አንስታ ታቅፈዋለች)

ተፈፀመ!